# በወንጀል ጉዳዮች የአተረጓጎም ልዩነት ያለባቸውን ድንጋጌዎች ላይ ወጥነት ያለው ትርጉም ለማምጣት እንዲቻል የተዘጋጀ የሕግ ማብራሪያ

**ማውጫ**

**ማውጫ** ........ ii
መግቢያ ........ 1
የሕግ ማብራሪያው ዓላማ ........ 2
የተፈፃሚነት ወሰን ........ 2
ምዕራፍ አንድ ........ 3
አከራካሪ የሆኑ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ላይ እና ልዩ ልዩ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ ........ 3
አከራካሪ የሆኑ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ ........ 3
1.1 በብሔራዊ ባንክ የምንዛሬ ተመን ያልወጣላቸው የውጭ ሀገር ገንዘቦችን ይዞ መገኘት የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትል ስለመሆኑ ፡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 346 ........ 3
1.2 የመንግስት የጥበቃ ሰራተኞች የወንጀል ተጠያቂነት፡ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 703 ይልቅ በአንቀጽ 420 ስር ክስ ሊቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ ........ 3
1.3 የወንጀል ህጉ አንቀጽ 453/1/ በተመለከተ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ስርዓት ላይ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል በሀሰት የተሰጠ መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ ካልተቻለ ክሱን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 446/ለ/ ስር ማቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ ........ 4
1.4 በወንጀል ህግ አንቀጽ 501 እና የህንጻ ደንብ 243/203 አንቀጽ 29(5) መሰረት የህንጻ ስራ መሪ/ተቋራጭ እና የሕንፃው ባለቤት እንደ የአግባብነቱ በወንጀል የሚጠየቁ ስለመሆኑ ........ 5
1.5 በወንጀል ህግ አንቀጽ 525(1) (ሀ) ስር የተጠቀሱትን ድርጊቶች ለራሱ ወይም ሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ የፈፀመ እንደሆነ ክስ ሊቀርብበት የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 525(4) መሰረት ስለመሆኑ ........ 6
1.6 የወንጀል ህጉ አንቀጽ 539/1/ሀ ላይ የተቀመጡት ማክበጃዎች እራሳቸውን ችለው በተናጠል ህጉን የሚያቋቁሙ ስለመሆኑ ........ 7
1.7 በወንጀል ህጉ አንቀጽ 543/3/ ስር ግልጽ የሆነ ደንብ እና መመሪያ መጣስ የሚለው የህጉ ማቋቋሚያ አደጋ የመድረስ አጋጣሚውን ከፍ የሚያደርጉ ጥሰቶችን በሚል ሊተረጎም የሚገባ ስለመሆኑ ........ 7
1.8 የወንጀል ህግ አንቀፅ 555፣ 556 እና 560 ተፈፃሚ ስለሚሆኑበት አግባብ ........ 8
1.9 የትራፊክ ደንብን በመጣስ በቸልተኛነት በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት በሚደርስበት ወቅት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572(1) መሰረት ክስ ሊመሰረት የሚገባው ስለመሆኑ፣ ........ 10
1.10 የወንጀል ህጉ አንቀጽ 577/3/ ላይ ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት የሚለው አስከ 3 ዓመት ቀላል እስራ ቅጣት የሚያስቀጣ በሚል ሊተረጎም የሚገባ ስለመሆኑ ........ 11
1.11 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1፣ 670 እና 713 ተፈፃሚ ስለሚሆኑበት አግባብ ........ 12
1.12 በእምነት ማጉደል ወንጀል እና በፍታብሔር ጉዳዮች መካከል ያለው ልዩነት እና የወ/ሕግ የአንቀጽ 675/3 ስለሚኖረው ተፈፃሚነት ........ 13
1.13 የወንጀል ህግ አንቀፅ 675 እና 692 ተፈፃሚ ስለሚሆኑበት አግባብ ........ 13

1.14 በመሸሸግ ወንጀል ተጠርጣሪው ንብረቱ የተገኘው በአንድ ንብረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል ምክንያት መሆኑን እንደሚያውቅ ወይም ማወቅ እያለበት የሸሸገ ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ የሚገባው ስለመሆኑ፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 682 ....15

1.15 የኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 እና 712ን በተመለከተ በአራጣ ምክንያት የተሰጠ ገንዘብ የሌለው ቼክ በወንጀል ላያስጠይቅ ስለሚችልበት ሁኔታ ....16

1.16 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 702/1 በኤጀንሲዎች አማካኝነት በተቀጠሩ የጥበቃ ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆንበት አግባብ ....17

1.17 በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 712(1) ሀ ስር የአራጣ ወንጀል ተፈጽሟል የሚባለው ተበዳሪው የገንዘብ ችግር ያለበት መሆኑ እና አበዳሪው ይህን የተበዳሪውን ችግር በመጠቀም ለተበዳሪው በሕግ ከተፈቀደው ወለድ በላይ ያበደረ ስለመሆኑ በአንድነት (Cumulatively) ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ....18

ክፍል ሁለት ....19

የጦር መሳሪያ ብዛትን፣ የመሸጋገሪያ ድንጋጌን እና ለግል መጠቀሚያ ከውጭ አገር የሚገባን የጦር መሳሪያ አስመልክቶ አዋጅ ቁ. 1177/12 ሊተረጎም ስለሚገባው አግባብ ....19

ምዕራፍ ሁለት ....22

ከኢኮኖሚ ነክ የወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የአተረጓጎም ልዩነት የፈጠሩ ድንጋጌዎችና በጉዳዮቹ ላይ የተሰጠ ማብራሪያ ....22

2.1. የንግድ ውድድር እና ሸማቾች መብት ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/06 አንቀጽ 24/1 እና 43 የተፈጻሚነት ሁኔታ....22

2.2. የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 (በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻለው) እና የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ሕግጋት ላይ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች መሪ/ስራ አስኪያጅ በመሆን ብቻ በወንጀል የሚጠየቅበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ....23

2.3. በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ተወካይ እና የባለቤት/የግለሰብ ነጋዴ/ ተወካይ የወንጀል ተጠያቂነት ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ....24

2.4. የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 118 እስከ 122 እና 125 የሚፈጸሙበት ሁኔታ....25

2.5. የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀፅ 120 (1) እና አንቀፅ 131 (1(ለ)) የተፈፃሚነት አግባብ....28

ምዕራፍ ሶስት....29

ከሙስና ወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የአተረጓጎም ልዩነት የፈጠሩ ድንጋጌዎችና በጉዳዮቹ ላይ የተሰጠ ማብራሪያ....29

3.1 በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደ ህዝባዊ ድርጅት ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ....29

3.2 ከባድ የሙስና ወንጀል ብሎ ክስ ለማቅረብ የተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ታሳቢ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ:- አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9 (2)....30

3.3 አቃቢ ፖሊሶች በሚያጅቧቸው እስረኞች ላይ የሚፈፅሙትን ድብደባ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ሳይሆን በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ክስ ማቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ ....30

3.4 በስልጣን አላግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተፈፀመ የሚባለዉ የተሰጠዉን ስልጣን አላግባብ በመጠቀም (Abuse) በማድረግ የተፈፀመ ሲሆን፣ ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት ግን ባለዉ ስልጣን ወሰን ሲፈፀም ስለመሆኑ:- አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9 እና አንቀፅ 13 (1) (ሐ).....................31

3.5 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 15 (1) (ለ) እና አንቀፅ 31) ላይ የተጠቀሰው "በአደራ የተረከበዉ ወይም የሚጠብቀዉ" የሚለዉ ፍሬ ነገር ለሁለቱ ድንጋጌዎች የሚኖረው ተፈፃሚነት........................32

3.6 ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠርና መገልገልን በተመለከተ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/07 አንቀፅ 23/3/ ወይም በወንጀል ህጉ አንቀፅ 378 እና 385 ድንጋጌዎች መሰረት ክስ ስለሚቀርብበት አግባብ ....32

3.7 የኩነቶች ምዝገባ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፤ወደ ሀሰት መለወጥ ወይም መጠቀምን በተመለከተ ከሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/07 አንቀፅ 23 ይልቅ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና በብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ 760/2004 አንቀፅ 66 ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ .....................................................................34

3.8 በሙስና የማታለል ወንጀልና ከሙስና ወንጀል ውጭ ሌሎች የማታለል ወንጀሎችን በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 32 እና የወንጀል ህግ አንቀፅ 696 የተፈፃሚነት ሁኔታ............................34

ምዕራፍ አራት............................................................................. ...................................36

ከወንጀል ስነ-ስርዐት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የአተረጓጎም ልዩነት የፈጠሩ ድንጋጌዎችና በጉዳዮቹ ላይ የተሰጠ ማብራሪያ ................................................................................................................36

4.1 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 60(ሐ) በአንቀጽ 665(1) እና 559(2) ላይ ስለሚኖረው ተፈፃሚነት...........36

4.2 በዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የሕጋዊ መከላከል መስፈርቶች ከተሟሉ ክስ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ..37

4.3 ፈጻሚው ባልታወቀ ተጠርጣሪ ላይ የተጣራ የምርመራ መዝገብ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 42(1) (ሀ) መሰረት ሊዘጋ የሚገባው ስለመሆኑ........................................................................................................37

4.4 በህግ በግልፅ ባልተፈቀዱ ጉዳዮች የተከሳሽ የቀድሞ ጥፋተኛነት ለዋስትና ክርክር መነሳት የሌለበት ስለመሆኑ................................................................................................................................38

4.5 ተከሳሽ በሌለበት ክሱ እንዲታይ በሚቀርብ አቤቱታ የግድ ተከሳሹ የተከሰሰበት ክስ መነሻ ቅጣቱ አስራ ሁለት አመት ጽኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ስላለመሆኑ፡ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161/2/ሀ...........39

4.6 በጊዚያዊነት በሚሰጡ ትእዛዞች ላይ ይግባኝ ስለሚጠየቅበት ሁኔታ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር184 .................................................................................................................................41

የትዕዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 184 ..................................................................41

የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አተቋም ...................................................................................................42

4.7 በወንጀል ህጉ በግልጽ በግል አቤቱታ ከሚቀርቡ ወንጀሎች ውጪ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች በእርቅ የማይቋጩ ስለመሆናቸው፡ የእርቅ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2012፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 211፣ 212፣ 664፣580 እና 590(1) ..........................................................................................................43

## መግቢያ

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተቋምን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት በማድረግ ከተደራጁት የስራ ክፍሎች ውስጥ የኢንስፔክሽ ክፍል አንዱ ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 6 (13) ላይ እንደተመለከተው የዚህ የስራ ክፍል ሚና በዐቃቤያነ ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ መለየት፣ በተገኘው ግኝት መሰረት ጉድለቶች እንዲታረሙ ማድረግ፣ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግና መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋት ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በተለያዩ የተቋሙ የስራ ክፍሎች ላይ የኦዲት ስራዎች ሲሰሩ ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል በተመሳሳይ ጉዳይ የተለያየ የሕግ አንቀፅ መጠቀም፣ የምርመራ ስራን ወይም ክርክርን ለመምራት የሚያስችሉ የወንጀል ስነስርዓት አንቀፆች ላይ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎም አለመከተል ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ፍትሕ የሚያዛቡ ችግሮችን ለመቅረፍ እና በባለሙያው መካከል ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ለማድረግ ከጠ/ዓ/ሕግ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች፣ ዳይሬክቶሬቶች እና ፅ/ቤቶች የአተረጓጎም ልዩነት እየፈጠሩባቸው ያሉ አከራካሪ የህግ ጉዳዮች በማሰባሰብ የሕግ ማብራሪያ ሊዘጋጅባቸው የሚችሉትን የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን በተጨማሪም በማብራሪያው ላይ ሌሎች መካተት የሚገባቸው ጉዳዮችን እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ከየስራ ክፍሉ በቂ እውቀትና ልምድ ያለው ባለሙያ በማሳተፍ ረቂቅ ሀተታው (commentary) እንዲዘጋጅ የተደረገ ሲሆን ይህ ረቂቅ ሲዘጋጅ አከራካሪው የህግ ጉዳይ ላይ የተያዙ ቃለጉባኤዎችን፣ ሀተታ ዘምንያቶችን፣ የሰበር ውሳኔዎችን፣ በጉዳዩ ላይ የውጭ ሀገራት ያላቸው ተሞክሮ እና የተለያዩ ፅሁፎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ የሕግ ማብራሪያው ረቂቅ ከተዘጋጀ በኋላ በተቋሙ ውስጥ ያሉ የስራ ክፍሎች አስተያዬት እንዲሰጡበት በማድረግ ተገቢ ሆነው የተገኙ አስተያየቶችን እንደ ግብአት በመጠቀም ይህ የህግ ማብራሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ ውጭ ይሄን ማብራሪያ በጥልቀት ለመረዳት የሚያስችል ዝርዝር የማብራሪያ ሰነድም ተዘጋጅቷል፡፡

በመሆኑም ዐቃቤያነ ሕግ ይህን የሕግ ማብራሪያ እና ይህን ማብራሪያ በጥልቀት ለመረዳት እንዲያስችል በአባሪነት የተያያዘውን ዝርዝር የማብራሪያ ሰነድ በምርመራ፣ ክስ በመመስረት እና በክርክር ሂደት ላይ ተግባራዊ በማድረግ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተቋም ወጥ እና ተገማች የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ የስራ መመሪያ የተሰጠ ሲሆን በተሰጠው መመሪያ መሰረት በመፈፀም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ በሂደት መፍትሄ የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

**የሕግ ማብራሪያው ዓላማ**

- በተቋሙ ውስጥ ባሉ የተለያዩ የስራ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ዓቃቤያነ ሕግ በአከራካሪ የሕግ ጉዳዮች ላይ ወጥ የሆነ አተረጓጎም እንዲከተሉ ማድረግ
- ለትርጉም የተጋለጡ የወንጀል ነክ ድንጋጌዎች ላይ ማብራሪያ መስጠት
- ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች እና ዳይሬክቶሬቶች የተዘጋጀውን የሕግ ማብራሪያ  በሚወስኑት ውሳኔ ከግምት እንዲያስገቡ ማስቻል
- ዓቃቤያነ ሕግ ምርመራ ሲመሩ፣ ክስ ሲመሰርቱ እና ክርክር ሲያካሂዱ የተዘጋጀውን የሕግ ማብራሪያ ተከትለው ስራቸውን እንዲያከናውኑ ማስቻል
- ለትርጉም የተጋለጡ የሕግ ድንጋጌዎች እና አሰራሮች በሚያጋጥሙበት ግዜ በተቋም ደረጃ ማብራሪያ የሚሰጥበትን ልምድ እንዲዳብር ማድረግ
- የዓቃቤያነ ሕግ ውሳኔዎች ከሕግ አውጪው አሳብ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማስቻል

**የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ የሕግ ማብራሪያ በሁሉም የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ውስጥ ባሉ የስራ ክፍሎች የሚሰሩ ዓቃቤያነ ሕግ የወንጀል ምርመራ ሲመሩ፣ ክስ ሲመሰርቱ፣  ክርክር ሲያካሄዱ እና ማናቸውንም የዓቃቤ ሕግ ስራ ወይም ተግባር በሚያከናውኑበት ወቅት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

### አከራካሪ የሆኑ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ላይ እና ልዩ ልዩ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ

### ክፍል አንድ

### አከራካሪ የሆኑ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ

**1.1 በብሔራዊ ባንክ የምንዛሬ ተመን ያልወጣላቸው የውጭ ሀገር ገንዘቦችን ይዞ መገኘት የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትል ስለመሆኑ ፡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 346**

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** በሀገራችን የምንዛሬ ዋጋ እውቅና ያልተሰጣቸው እና የማይመነዘሩ የውጭ ምንዛሬዎችን /የውጭ ገንዘብ ይዞ የተገኘ ሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 346 መሰረት ክስ ሊቀርብበት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን በተመለከተ የተለያ አረዳድና ውሳኔ መኖር

**የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 591/2000 እና አዋጁን ለማስፈፀም መስከረም 25/2010 የወጣው መመሪያ ቁጥር FXD /34/49/2017 በማየት አዋጁ ያስቀመጠው ትርጉም "የውጭ አገር ገንዘብ ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ በማናቸውም ሃገር ህጋዊ ገንዘብ የሆነ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ብሄራዊ ባንክ ያሳወቀው ማናቸውም ገንዘብ ነው" በሚል ትርጉም ተሰጥቶት የሚገኝ በመሆኑ በዚህ ትርጉም መሰረት አንድ የውጭ አገር ገንዘብ በኢትዮጵያ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሁለት መሰረታዊ ነገሮች ማለትም በሌላ ሃገር ህጋዊ የሆነ ገንዘብ መሆን እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ ለክፍያ ያሳወቀው መሆን አለበት የሚለውን ሚሟላት እንደሚጠበቅበት ግንዛቤ የሚሰጥ ነው፡፡ እነዚህ በአዋጁና በመመሪያው የተገለፀት ሁለቱ መስፈርቶች ተሟልተው የተገኙ ከሆነ የውጭ አገር ገንዘብ ይዞ የተገኘ ሰው ላይ ክስ ማቅረብ እንደዚሁም የሌላ አገር ገንዘብ ሆኖ ነገር ግን ተጠርጣሪው የውጭ አገር ገንዘብ ይዞ በተገኘበት ዕለት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ያላሳወቀው እና የዕለት ምንዛሪው ስንት እንደነበረ ያልተገለፀበት ማናቸውም ገንዘብ ከሆነ ክስ ሊቀርብ አይገባም፡፡

**1.2 የመንግስት የጥበቃ ሰራተኞች የወንጀል ተጠያቂነት፡ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 703 ይልቅ በአንቀጽ 420 ስር ክስ ሊቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** የወንጀል ህጉ አንቀጽ 420 የስራ ሃላፊነትን ባለመወጣት በመንግስት ሰራተኞች የሚፈጸም ወንጀል በሚል የሚያስቀምጥ ሲሆን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 703(2) መሰረት ደግሞ በሌላ

ሰው የስራ አመራር ላይ የሚፈጸመው ጉዳት በመንግስት ወይም በህዝብ ንብረት ላይ ከሆነ በሚል ተመሳሳይነት ያላቸው ድንጋጌዎች መኖራቸው ድርጊቱን ፈጸመ የተባለው ግለሰብ የመንግስት የጥበቃ ሰራተኛ ሆኖ በሚጠብቀው ንብረት ላይ ወንጀል ፈጽሞ ሲገኝ እነዚህን ድንጋጌዎች መነሻ በማድረግ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የወጥነት ችግር ይታይባቸዋል፡፡

**የጠቅላይ አቃቤ ህግ አቋም**

የመንግስት ሰራተኛ የሆነ ሰው ለሚፈጽመው ወንጀል የመንግስት ሰራተኛን የተመለከቱ ድንጋጌዎች በተለየ መልኩ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡የወንጀል ህጉ አንቀጽ 703 የሚገኘው እንደ አጠቃላይ የንብረት መብቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ስር በመሆኑና የወንጀል ህጉ አንቀጽ 420 ደግሞ በመንግስት ሰራተኞች የሚፈጸሙ ወንጀሎች ስር የሚገኝ በመሆኑ አንድ የጥበቃ ሰራተኛ በሚጠብቀው የመንግስት መስሪያቤት ላይ በሚፈጽመው ወንጀል ለሚከተለው የወንጀል ሃላፊነት ልዩ የሆነው ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 420 ይሆናል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 703 የተፈጻሚነት ወሰን ደግሞ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ውጪ ባሉ ሌሎች ድርጅቶች ውስጥ የጥበቃ ሰራተኞቻቸውን ጨምሮ የሚሰሩ ሰራተኞች በድርጅቱ ላይ ለሚፈጽሙት የወንጀል ተግባር ብቻ ይሆናል፡፡

**1.3 የወንጀል ህጉ አንቀጽ 453/1/ በተመለከተ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ስርዓት ላይ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል በሀሰት የተሰጠ መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ ካልተቻለ ክሱን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 446/ለ/ ስር ማቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ**

አከራካሪው ጉዳይ፡- ማብራሪያ ያስፈለገው ምስክሮች ለፖሊስ የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመለወጥ ለፍርድ ቤት የተለየ ምስክርነት ቃል በሚሰጡ ጊዜ የተወሰኑት ዐቃብያነ ህግ በወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ሲከሱ ሌሎቹ ደግሞ በወ/ህ/ቁ 446/ለ/ ክስ የሚያቀርቡ በመሆኑ የክስ አመሰራረት ወጥነት ችግር በማጋጠሙ ነው

**የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

አንድ ምስክር ለፖሊስ የሰጠው ቃል ለፍርድ ቤት ከሰጠው ቃል ጋር ልዩነት ሲኖር ከቃሎቹ አንዱ ሃሰተኛ እንደሆነና አንዱ ደግሞ እውነት መሆኑ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ትክክል ያልሆነው መረጃ በትክክል የትኛው እንደሆነ ማወቅ ሲቀር በአቃቤ ህግ በኩል ሁለት የተለያዩ የምስክርነት ቃሎች መስጠቱን ካረጋገጥን ለፖሊስም ይሁን ለፍ/ቤት (ለባለስልጣኖች) የተሳሳተ መረጃ ማቅረቡ በወንጀል ሊያስቀጣ የሚገባውና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 446/ለ/ ሊሸፈን የሚችል በመሆኑ በምስክሮች (የመዝገቡን ውጤታማነት ሊጎዳ የሚችል) የቃል መቀየር በተከሰተ ጊዜ ለፍርድ ቤት የሰጡት ቃል

ሃሰተኛ መሆኑን በተለያዩ ማስረጃዎች ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት ካልተቻለ በቀር ክሱን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 446/ለ/ ስር ማቅረብ ይገባል፡፡

**1.4 በወንጀል ህግ አንቀጽ 501 እና የህንጻ ደንብ 243/203 አንቀጽ 29(5) መሰረት የህንጻ ስራ መሪ/ተቋራጭ እና የሕንፃው ባለቤት እንደየአግባብነቱ የሚጠየቁ ስለመሆኑ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** በወንጀል ህግ አንቀጽ 501 እና የህንጻ ደንብ 243/203 አንቀጽ 29(5ሀ) መሰረት ተደርጎ ክስ ሲቀርብ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ከፊል ዓ/ሕግ የህንጻ ስራ መሪ/ተቋራጭን ተከሳሽ ሲያደርግ ከፊል ዓ/ሕግ ደግሞ የሕንፃውን ባለቤት ተከሳሽ ያደርጋል ይህም የውሳኔ ወጥነት ችግር ፈጥሯል

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

የሕንፃ ደንብ ቁጥር 243/2003 አንቀፅ 29(5) ስር የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች በባህሪቸው በከፊል የሕንፃው ባለቤት የሚመለከቱ ሲሆኑ ከፊሎቹ ደግሞ የስራ ተቋራጩን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለማሳያ ያህል አንቀፅ 29(5ሠ) ስር በግንባታ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞችና ጎብኚዎች የደህንነት መጠበቂያዎችን ማሟላት በሚል የተገለፀው ኃላፊነት ሰራተኞቹን በተመለከተ የስራ ላይ ደህንት መጠበቂያዎችን ማሟላት የአሰሪዎች(ሕንፃውን የሚያሰራው ግለሰብ ወይም ስራው በተቋራጭ የሚሰራ ከሆነ ደግሞ የተቋራጩ) አንዱ ግዴታ ሲሆን ጎብኚዎችን በተመለከተ አስጎብኚው የሕንፃው ባለቤት ወይም ወኪሉ ስለሆነ የጎብኚዎች ደህንነታቸውን የመጠበቅ ሃላፊነት በባለቤቱ ላይ እንደሚወድቅ ያደርገዋል፡፡የደንቡ አንቀፅ 29(5ሀ) የአዋጁ አንቀፅ 31(3) ተከታይ ስለሆነ እና አዋጁ ላይም ሃላፊነቱን ለሕንፃው ባለቤት የሰጠ በመሆኑ ደንቡ ላይ የተቀመጠው ግዴታ በሕንፃው ባለቤት የሚፈፅመው ተግባር ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ቁፋሮን በተመለከተ የደንቡ አንቀፅ 29(5ለ) የአዋጁ አንቀፅ 31(4) ጋር ተያያዥነት ስላለውና በአዋጁ የግንባታ ቦታው ባለቤት ሃላፊነት እንደሚኖርበት ስለሚደነግግ ደንቡ ላይ የተቀመጠው ግዴታ በሕንፃው ባለቤት የሚፈፅመው ተግባር ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ አዋጁ በአንቀፅ 32(1) ላይ ሕንፃ ሲገነባ በሕዝብ ላይ ከፍተኛ መጉላላት ወይም አደጋ እንዳያደርስ ለማድረግ የግንባታ ቦታው ባለቤት የመከላከያ እርምጃዎች የመውሰድ ሃላፊነት እንደሚኖርበት ስለሚያስቀምጥ ከዚህ ሃሳብ ጋር የተገናኘው የደንቡ አንቀፅ 29(5ሐ፣5ሰ)ም የሕንፃው ባለቤት ሃላፊነት ተደርጎ መተርጎም አለበት፡፡ የህንፃው ስራ በስራ ተቋራጭ የሚሰራ ከሆነ በደንቡ አንቀፅ 29(መ እና ረ) የተመለከተው ሃላፊነት በቀጥታ የሚመለከተው የስራ ተቋራጩን በመሆኑ ክስ ሲመሰረት ይህን ከግምት በማስገባት መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ የሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 አንቀፅ 47(2) የወንጀል ሕጉን ተፈፃሚነት የጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎች ላይ የሚገደብ መሆኑን ስለደነገገ አዋጁ በግልፅ በሸፈናቸናቸው የወንጀል ጉዳዮች ላይ ዓ/ሕግ ይህን አዋጅ ጠቅሶ ክስ

ማቅረብ የሚገባው ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ ጉዳዮች ሆነው በደንብ ቁጥር 243/2003 ላይ የተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ደግሞ ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ተከትሎ የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 501ን በጣምራነት በመጠቀም ክስ ማቅረብ ይገባል፡፡

## 1.5 በወንጀል ህግ አንቀጽ 525(1) (ሀ) ስር የተጠቀሱትን ድርጊቶች ለራሱ ወይም ሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ የፈፀመ እንደሆነ ክስ ሊቀርብበት የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 525(4) መሰረት ስለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ-** የወንጀል ህግ አንቀጽ 525(1) እና 525(4) ድንጋጌዎች በንኡስ አንቀጾቻቸው ላይ መርዛማ ነገሮችን ወይም ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶችን ወይም እጾችን ….ያበቀለ፤ የገዛ ፤የሰራ ፤ይዞ የተገኘ፤የሰጠ… የሚሉ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችን ማካተታቸው በአቃቢያን ህጎች መካከል የውሳኔ ወጥነት ችግር አስከትሏል፡፡
አንዳንድ ዐቃብያነ ህጎች እነዚህን በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር እንዳይመረቱ፤ እንዳይሰሩ፤ እንዳይዘዋወሩና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ ነገሮች ተጠርጣሪው ያበቀለው፤ የገዛው፤ የሰራው፤ ይዞ የተገኘው፤ የሰጠው ለግል ጥቅም ነው ወይስ ለሌላ አገልግሎት የሚለው ከግምት ሳይገባ ከሁለቱ ድንጋጌዎች በአንዱ ክስ የሚያቀርቡ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ተጠርጣሪው የተከለከለውን ነገር ያበቀለው፤ የገዛው፤ የሰራው፤ ይዞ የተገኘው፤ የሰጠው ለምን አላማ እንደሆነ መረጋገጥ አለበት በሚል ለራሱ ወይም ሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ ከሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 525(4) ክስ ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 525(1) መሰረት ክስ ማቅረባቸው የወጥነት ችግር እንዲስተዋል አድርጓል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

እንደ ጠቅላይ አቃቤ ህግ አንድ ሰው በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ያበቀለው ፤ የገዛው ፤የሰራው ፤ይዞ የተገኘው፤የሰጠው መርዛማ ነገር ወይም ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እጽ እራሱ ወይም ሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ መሆኑን ማስረጃዎች ካረጋገጡ ክስ ሊቀርብ የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 525(4) መሰረት ሊሆን ይገባዋል፡፡ከዚህ ውጪ ባሉ ሁኔታዎች በህጉ መሰረት በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር እነዚህን ክልከላ የተጣለባቸውን ነገሮች ማብቀል፤ መግዛት፤መስራት፤ይዞመገኘት የሚያስቀጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 525(1) እና ሌሎች የድንጋጌው ንኡሳን አንቀጾች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

**1.6 የወንጀል ህጉ አንቀጽ 539/1/ሀ ላይ ተቀመጡት ማክበጃዎች እራሳቸውን ችለው በተናጠል ህጉን የሚያቋቁሙ ስለመሆኑ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** የአገዳደሉ ሁኔታ አሰቃቂ ባልሆነበት ጊዜ ቀድሞ በነበረ የመግደል ሃሳብ ወይም ዝግጅት የተፈጸመ ግድያ ብቻ ተሟልቶ ሲገኝ በህጉ ላይ የተጠቀሱት ሌሎቹ መቋቋሚያ ነጥቦች ካልተሟሉ በህጉ ድንጋጌ ስር ልንከስ አይገባም የሚል በየአንደአንድ አቃብያነ ህግ አቋም ሲሆን በሌሎች ደግሞ ድንጋጌው ላይ የተዘረዘሩት የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች በተናጠል ሊቆሙ የሚችሉ ቢሆንም ሁሉም ነጥቦች ላይ ግን ገዳዩን በተለይ ጨካኝ ነውረኛ ወይም አደገኛ ሊያስብሉት ይገባል በሚል አቋም በመያዝ ወጥ የሆነ የወንጀል ክስ አመሰራረት ችግር የፈጠረ በመሆኑ ነው፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

ከባድ ግድያ ላይ የሚገኙት ማቋቋሚያ ነጥቦች እራሳቸውን ችለው እንደሚቆሙ ገልጸው በተለይ ማስረጃዎች ቀድሞ የነበረን የመግደል ሃሳብ የሚያሳዩ ከሆነ ሌላ ሁኔታዎችን መመልከት ሳያስፈልግ በከባድ ግድያ ክስ ሊቀርብ እና ሊያስቀጣ እንደሚችል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በተጨማሪም በድንጋጌው ላይ ማክበጃዎቹ የተጠቀሱበት አግባብ ሲታይ በነጠላ ሰረዝ መሆኑን እያንንዳንዱ ማክበጃዎች እራሳቸውን ችለው የቆሙና በወ/ህጉ አንጽ 539/1//ሀ ለማቋቋምም ሆነ ለመክሰስ በቂ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ ቀድሞ በነበረው ሃሳብ ወይም ዝግጅት እና በግድያው መካከል የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት መኖሩ ሲረጋገጥና ግድያው የተፈጸመው ቀድሞ ታስቦ ወይም በቂም ምክንያት መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች በተሟሉ ጊዜ አገዳደሉ የትኛውንም አይነት ቢሆን እንኳን ክስ ሊቀርብ የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539/1/ሀ ሊሆን የሚገባና በድንጋጌው ላይ የተቀመጡት ሌሎቹ ማክበጃዎች ደግሞ ነውረኛ አደገኛ ወይም ጭካኔን በሚያሳይ መልኩ የተፈፀሙ ሲሆን እራሳቸውን ችለው በተናጠል ህጉን የሚያቋቁሙ በመሆናቸውም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539/1/ሀ ክስ ሊመሰረት ይገባል፡፡

**1.7 በወንጀል ህጉ አንቀጽ 543/3/ ስር ግልጽ የሆነ ደንብ እና መመሪያ መጣስ የሚለው የህጉ ማቋቋሚያው አደጋ የመድረስ አጋጣሚውን ከፍ የሚያደርጉ ጥሰቶችን በሚል ሊተረጎም የሚገባ ስለመሆኑ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** በድንጋጌው ላይ ደንብ ወይም መመሪያ የሚለው ማንኛውንም ህግ ለማለት ነው ወይስ የግድ ደንብ ወይም መመሪያ መሆን አለበት በሚል እና ሁሉም የትራፊክ አደጋ የሚከሰተው ከደንብ መተላለፍ ሲሆን አሁን ባለው ሁኔታ ዐቃቤ ህጉ ደንብ መተላለፍ ሲኖር የተወሰነው በ543/3/ ክስ ሲያቀርብ የተወሰነው ደግሞ በ543/2/ ክስ ያቀርባል በሚል ነው፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

የህጉ የአማርኛው ቅጂ ገዢ እንደሚሆን የሚታወቅ ቢሆንም የህጉ አላማ የግድ ደንብ ወይንም መመሪያ ብቻ የተላለፈን የሚል ትርጉም እንዲሰጠው ሳይሆን ሌሎች ከመመሪያ እና ከደንብ በላይና በታች የሆኑትም ህጎች የሚጨምር በመሆኑና በተከሳሾች መሃል እኩልነትን መሰረት ያደረገ የክስ አቀራረብ ሊኖር ስለሚገባ ከባድ የማይባሉ ደንቦችን ጥሶ ተገኝቶ ሰው ቢሞት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 543/3/ ስር ክስ ማቅረቡ ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታና ከርትዕም አንጻር ተገቢ ባለመሆኑ በህጉ ድንጋጌ ሊከሰሱ የሚገባቸው ሁኔታዎች መለየት አስፈላጊ መሆኑ በመታመኑ በከባድ ቸልተኝነት በንዑስ አንቀጽ 3 ስር ክስ ሊቀርብባቸው ይገባል የተባሉ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ከፍጥነት በላይ ማሽከርከር፣በተቃራኒ መንገድ ላይ መንዳት፣በእግረኛ መንገድ ላይ ሰው መግጨት (ሁኔታዎች ሳያስገድዱት ሆነ ብሎ በመሄድ)፣የትራፊክ መብራት በመጣስ ማሽከርከር፣ያለ መንጃ ፍቃድ ማሽከርከር፣እግረኛ ማቋረጫ ላይ ሰው መግጨትን እና **በእነዚህ ደረጃ አደጋ የመድረስ አጋጣሚውን ከፍ የሚያደርጉ ጥሰቶችን** ጨምሮ ያሉ ደንብ ወይም መመሪያ መተላለፎች በአንቀጽ 543/3/ ስር ክስ ሊቀርብባቸው ይገባል። ሆኖም ግን ከላይ ከተዘረዘሩት እና ተመሳሳይነት ካላቸው ደንቦች ውጪ ተላልፎ በቸልተኝነት ሰውን የገደለ በንዑስ አንቀጽ 2 ስር ክስ ሊቀርብበት ይገባል።

## 1.8 የወንጀል ህግ አንቀፅ 555፣ 556 እና 560 ተፈፃሚ ስለሚሆኑበት አግባብ

**አከራካሪዉ ጉዳይ፡-** ከፊሎቹ ባለሞያዎች የእጅ እልፊት ወንጀል የሚፈፀመዉ በእጅ ብቻ ነዉ ብለዉ ሲያምኑ ሌሎቹ ደግሞ የተፈፀዉ የወንጀል ድርጊት የሚለየዉ ከተገኘዉ ወይም ለማስገኘት ከታሰነዉ የወንጀል ዉጤት ላይ በመመርኮዝ ነዉ ብለዉ ያምናሉ።

**የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

የወንጀል ድንጋጌዎቹን በአግባቡ በስራ ላይ ለማዋልና በተግባር የሚስተዋሉ የዉሳኔ ልዩነቶች ለመቅረፍ ባለሞያዉ ዉሳኔዎችን በሚሰጥበት ወቅት የሚከተሉትን ነገሮች ከግምት ወስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

I. **ሶስቱም አንቀፆች በአካል ላይ በደረሰዉ የጉዳት መጠን ብቻ የሚለያዩ ስለመሆኑ፡**

የአንቀፆቹ ይዘት በንፅፅርና በጥልቀት በማየት ለመረዳት እንደሚቻለዉ ሶስቱንም የህግ ድንጋጌዎች የሚለያዩት የደረሰዉን የጉዳት መጠን መሰረት በማድረግ ብቻ ነዉ። ይህም ሲባል አንድ ግለሰብ በሌላ ሰዉ አካል ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ግለሰቡ ሊከሰስ የሚገባዉ ከሶስቱ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች በየትኛዉ ነዉ የሚለዉ ጥያቄ የሚመለሰዉ የጉዳቱን መጠን መሰረት በማድግ ብቻ ነዉ። የአንቀፆቹን ይዘት በአግባቡ ለመረዳት የሶስቱንም የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ይዘት ስንመለከት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 555 መሰረት ከባድ አካል ጉዳት ተፈፀመ የሚባለዉ "የተጎጂዉን ሕይወት በሚያሰጋ ወይም በሰዉነቱም ሆነ በአዕምሮዉ ላይ ለዘወትር ጠንቅ በሚያተርፊ ሁኔታ ጉዳት ካደረሰ ወይም የሌላ ሰዉን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑት ብልቶቹ ወይም ከህዋሳቶቹ አንዱን የጎደለ ፣ እንዳያገለግሉ ያደረገ ወይም በሚሳሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ መልኩን ያበላሸ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ ከባድ የሆነ ጉዳትን ያስከተለ እንደሆነ ነዉ" በማለት ሲደነገግ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 556 ደግሞ ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀል ማለት

*"…………በአንቀፅ 555 ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉጪ በሰዉ አካል ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ነዉ፡፡"* በማለት ይደነግጋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 560 መሰረት የእጅ እልፊት ተፈፀመ የሚባለዉ ደግሞ

"…..የአካል ጉዳትን ወይም የጤና ጉድለትን ሳያደርስ በሌላ ሰዉ ላይ የእጅ እልፊት ወይም የመጋፋት ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ ነዉ፡፡" በማለት የደነገገ ሲሆን አንቀፁ አክሎም "ሰንበሮች፣ የደም መቋጠር ምልክቶች ወይም በቶሎ የሚያልፍ ህመም ይም ሥቃይ እንደ አካል ጉዳት ወይም እንደ ጤና ጉድለት አይቆጠሩም" በማለት ይደነግጋል፡፡

ከላይ የተገለፁት የወንጀል ድንጋጌዎች የወንጀል ድርጊቱን ሲደነግጉ ጉዳቱን ለማድረስ አገልግሎት ላይ የዋለዉ መሳሪያ ከግምት ዉስጥ ያላስገቡ ቢሆንም ብዙ ግዜ የጉዳቱን መጠን ወደጎን በመተዉ ጉዳቱ የደረሰበትን መሳሪያ ብቻ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ክስ ሲመሰርት ይታያል ነገር ግን ሶስቱም የህግ ድንጋጌዎች ከ 556(2) ዉጪ ያሉት የተመሰረቱት በደረሰዉ የጉዳት መጠን እንጂ ጉዳቱን ለማድርስ በተጠቀሙት የመሳሪያ አይነት ላይ አይደለም፡፡ በተለይ ደግሞ የወ/ህ/ቁ 560 ንዑስ አንቀፅ 1 ሶስተኛዉ ዓ.ነገር ላይ

" ቀላል የሆኑ ሰንበሮች፣የደም መቋጠር ምልክቶች፣ወይም በቶሎ የሚያልፍ ህመም ወይም ስቃይ እንደ አካል ጉዳት ወይም የጤና ጉድለት አይቆጠሩም"

የሚለዉን አገላፅ የእጅ እልፊት ወንጀል በእጅ ብቻ ሳይሆን በመሳሪያም ሊፈፀም እንደሚችል ለመረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለፅ ጉዳቱን ለማድረስ የተጠቀመዉ መሳሪያ ምንም ይሁን ምንም ድርጊቱ ያስከተለዉ ጉዳት ቀላል የሆኑ ሰንበሮች፣የደም መቋጠር ምልከቶች፣ወይም በቶሎ የሚያልፍ ህመም ወይም ስቃይ እንደሆነ በእጅ እልፊት ስር ሊመደብ እንደሚገባ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሌላዉ ብዙዎች የሚያነሱት መከራከሪያ የወ/ህ/ቁ 560 ርዕሱ የእጅ እልፊት ማለቱ በራሱ ድርጊቱ መፈፀም ያለበት በእጅ መሆኑን ያመለክታል የሚል ቢሆንም ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረዉ ቀላል የሆኑ ሰንበሮች፣የደም መቋጠር ምልከቶች፣ወይም በቶሎ የሚያልፍ የህመም ወይም ስቃይ እንደ አካል ጉዳት ወይም የጤና ጉድለት አይቆጠሩም ማለቱ የእጅ አልፊት የሚለዉ የድንጋጌዉ ርዕስ

የሚያደርሰዉ በቀላል የሚያልፍ ህመም መሆኑን እንጂ በእጅ ብቻ መፈፀም እንዳለበት አያመለክትም፡፡

II. የደረሰዉ የጉዳት መጠን ሳይሆን ጉዳት አድራሹ ለማድረስ ያሰበዉን የጉዳት መጠን አብሮ መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ፡- ብዙ ግዜ የሚስተዋለዉ ችግር ተከሳሹ ሊያደርሰዉ የፈለገዉ ጉዳት ከነገሮች ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ለመረዳትና በማስረጃ ለማስደገፍ እየተቻለ በደረሰዉ ጉዳት ላይ ብቻ በመመስረት ዉሳኔዎችን መስጠት ሌላዉ የችግሩ መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ ምንም እንኳን የደረሰዉ ጉዳት በእጅ እልፊት ወይም በቀላል አካል ጉዳት ስር የሚሸፈን ቢሆንም ከአጠቃላይ ነባራዊዉ ሁኔታ በመነሳት ማለትም፡ ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመዉ መሳሪያ ፣ የግል ተበዳዩ የሚገኝበት ሁኔታና የተከሳሹ ያለዉ ግንዛቤ ፣ ተበዳዩና ጉዳት አድራሹ ተነፃፃሪ ጉልበት ፣ የህክምና ምርመራ ዉጤት ፣ ከደረሰዉ በላይ ጉዳት ያልደረሰበት ምክንያት እና የመሳሰሉትን አከባቢያዊ ሁኔታዎችን በጋራ በመመዘን የተከሳሹ ድርጊት በታወቀ ወይም በተለመደ ሂደት (In the normal course of things) ሊያስገኝ የሚችለዉን ዉጤት ግምት ዉስጥ በማስገባት ተገቢ የሆነዉን ወሳኔ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ክስ ሲመሰረት ተከሳሹ የተጠቀመው መሳሪያ ብቻ በመመርኮዝ ሳይሆን ከአጠቃላይ ነባሪ ሁኔታ በመነሳት የደረሰውን ወይም ሊያደርስ ያሰበውን ጉዳት ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

### 1.9 የትራፊክ ደንብን በመጣስ በቸልተኛነት በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት በሚደርስበት ወቅት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572(1) መሰረት ክስ ሊመሰረት የሚገባው ስለመሆኑ፣

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** አንድ አሽከርካሪ የትራፊክ ደንብን በመጣስ በቸልተኝነት በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ሲያደርስ በአንድ በኩል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572(1) ተግባራዊ የሚሆነው ንብረትን ለአደጋ ስለ ማጋለጥ እንጂ ከማጋለጥ አልፎ ጉዳት የደረሰ ከሆነ ጉዳዩ የሚሸፈነው በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር ስለሆነና ይህ ድንጋጌ ደግሞ ለጉዳዩ አግባብ ያለው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌና የተጣሰው የትራፊክ ደንብ ድንጋጌ በተደራራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ የሚል ስለሆነ እንዲሁም በወንጀል ሕጉ በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ተጠያቂ ስለማያደርግ ክስ ሊመሰረት አይገባም የሚል መከራከሪያ ሲቀርብ በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572(1) ስር ክስ መመስረት ባይቻልም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 856 መሰረት ክስ ሊመሰረት ይገባል የሚል ክርክር ይነሳል፡፡ በተጨማሪም ምንም እንኳ የወንጀል ድርጊቱ ንብረቱን ለአደጋ ከማጋለጥ አልፎ በንብረቱ ላይ ጉዳት ያደረሰ ቢሆንም ዐቃቤ ሕግ በ572(1) መሰረት የትራፊክ ደንብን በመጣስ ለአደጋ ማጋለጥ ወንጀል ክስ ከመመስረት የሚከለክለው ሕግ የለም በማለት ክስ የሚመሰርቱ ዐቃቤያነ ሕጎች መኖራቸው ተስተውሏል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 856 ተግባራዊ የሚሆነው በአንቀጽ 689 እና 690(1) ስር ከተቀመጡት ሁኔታወች ውጭ የሌላ ሰውን ንብረት የማበላሸት ወይም ዋጋው እንዲቀንስ የማድረግ ተግባር ሲፈጸም እንጂ ሙሉ በሙሉ እንዳያገለግል በማድረግ ወይም ዋጋ በማሳጣት በደረሰ የንብረት ጉዳት ላይ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አንድ አሽከርካሪ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብን በመጣስ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ሲያደርስ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው በወንጀል ሕጉ 572(1) እና በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ(ከነማሻሻያው) ቁጥር 208/2003 እና 395/2009 አንቀጽ 5(4)(ሀ) መሰረት ነው፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱ የሰውን ንብረት ለአደጋ ከማጋለጥ አልፎ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(2) መሰረት ለጉዳዩ አግባብ ያለው የወንጀል ህጉ ድንጋጌና የተጣሰው የትራፊክ ደንብ ድንጋጌ በተደራራቢነት ተፈጻሚ የሚሆኑ መሆኑን መግለጹ ጉዳቱ ከደረሰ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከሚያስከስሰው በተደራቢነት ሌላ ክስ ሊያስከስስ የሚችል መሆኑን የሚጠቁም እንጂ ዐ/ሕግን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572(1) መሰረት ክስ ከመመስረት የሚያግደው አይደለም፡፡ ስለሆነም የሕጉ አላማ አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብን በመጣስ በንብረት ላይ የሚያስከትሉትን አደጋ ለመግታት የትራፊክ ደንብ እንዲከበር ጥበቃ ማድረግ ስለሆነና ራሱን ችሎም ቅጣት የሚያስከትል በመሆኑ ከማጋለጥ አልፎ ጉዳት ቢያደርስ በቸልተኛነት በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስን የሚመለከት ግልጽ ድንጋጌ ስለሌለ በአንቀጽ 572(2) መሰረት ተደራቢ/concurrent/ ክስ ማቅረብ ባይቻልም በ572(1) መሰረት ግን ክስ ሊመሰረት ይገባል፡፡

## 1.10 የወንጀል ህጉ አንቀጽ 577/3/ ላይ ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት የሚለው ቃል እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራ ቅጣት የሚያስቀጣ በሚል ሊተረጎም የሚገባ ስለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** ድንጋጌው ላይ ያስቀመጠው ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት እስራት 3 ዓመት ነው በሚል የተወሰው ዐ/ህግ አቋም የያዘ ሲሆን ልላው ደግሞ 25 ዓመት ጽኑ እስራትን በሚል በመተርጎም አቋም በመያዙ በህጉ አተረጓጎም ላይ ወጥነት ባለመኖሩ ነው፡፡

**የጠቅላይ ዐ/ህግ አቋም፡-** የወንጀል ህጉ ሃተታ ዘምክንያት ንዑስ ቁጥር ሶስት ላይ የቃላት ማስተካከያ ብቻ ተደርጎ እንደተረቀቀ የሚገልጽና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 549/3/ን ስንመለከት 5ኛ መስመር ላይ እነዚህ ቅጣቶች በደንበኛው ህግ ላይ ከፍተኛ ተብሎ እስከተወሰነው ቅጣት ለመድረስ ይችላሉ የሚል ሲሆን እነዚህ ቅጣቶች በሚል የተቀመጠው ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተቀመጡትን የሚያመላክትና ድንጋጌዎቹም ቀላል እስራትን የሚያመላክቱ በመሆኑ የቀላል እስራት መደበኛ ከፍተኛ ደግሞ ሶስት አመት ስለመሆኑ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 106/1/ ስለሚደነግግ የወንጀል

ህጉ አንቀጽ 577/3/ ላይ ከፍተኛው መደበኛ የሚለው ቅጣት እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራ ቅጣት ያስቀጣል በሚል ሊተረጎም ይገባል፡፡

## 1.11 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1፣ 670 እና 713 ተፈፃሚ ስለሚሆኑበት አግባብ

**አከራካሪው ጉዳይ፡** በስርቆት፣ ውንብድና እና በማስገደድ መጠቀም ወንጀል መሰረት ተደርጎ ክስ በሚቀርብበት ሰዓት በተለያዩ ቅ/ጽ/ቤቶችና ዳይሬክቶሬቶች የክስ አቀራረብ ልዩነት ችግር ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም የቅሚያ ወንጀል በአንድ ቅ/ጽ/ቤት በውንብድና ክስ የሚመሰረትበት ሲሆን፤ በሌላው ደግሞ በስርቆት ይቀርብበታል፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 እና 713 እንዲሁም የተቀመጡት መስፈርቶች ግልጽ ካለመሆናቸው የተነሳ በዐቃብያን ሕግ መካከል የአተረጓጎም ወጥነት የሌለ መሆኑን ተስተውሏል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

የመንጠቅ ድርጊት በሚፈጸምበት ወቅት በተበዳይ ላይ የኃይል ድርጊት ስለማይኖር ከስርቆት ወንጀል ጋር የሚስተካከል በመሆኑ በወንጀል ሕግ ቁጥር 665/1 ስር በተደነገገው መሰረት ክስ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ነገር ግን ውንብድና ማለት ስርቆትና የኀይል ድርጊት በአንድ ላይ ሲሟሉ የሚቋቋም በመሆኑ በወንጀል ሕግ 670 ላይ የኃይል ድርጊት የሚፈፀመው በንብረቱ ላይ ሳይሆን በሰው ላይ በመሆኑ በግል ተበዳዩ ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ዛቻና ማስፈራራት ከታከለበት በውንብድና ክስ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

ስለዚህ ተከሳሽ ዕቃ ለመውሰድ እንዲያመቸው ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኋላ የገጠመውን ተቃውሞ ውጤታማነት ለማስቀረት ሲል በሌላ ሰው ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ የማንገላታት ተግባር ወይም ከባድ ዛቻ የፈጸመ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ይህን ሰው ለመከላከል እንዳይችል ካደረገው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 በመተላለፍ ክስ ሊቀርብበት ይገባል፡፡

ከዚህ ባሻገር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 713 የተጠቀሰው ወንጀል የሚፈጸመው በዋናነት በሰነዶችና ሰነድን ከመሳሰሉ ዋጋ ያላቸው ነገሮች ላይ ሲሆን፤ ውንብድና ግን ንብረት ለመውሰድ ነው የሚፈጸመው፡፡ ስለዚህ በማስገደድ መጠቀም ወንጀል በግል ተበዳይ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ስነልቦናዊ ተጽእኖ በመፍጠር የሚፈጸም ሲሆን፤ ውንብድና ግን ቅጽበታዊ አካላዊ ጉዳት (immidiate physical damage) በማድረስ ወይም ለማድረስ በመቃጣት የሚፈጸም ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን መለያ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ አንደአግባብነቱ ክስ ሊቀርብ ይገባል፡፡

## 1.12 በእምነት ማጉደል ወንጀል እና በፍታብሔር ጉዳዮች መካከል ያለው ልዩነት እና የወ/ሕግ የአንቀጽ 675/3 ስለሚኖረው ተፈፃሚነት

**አከራካሪው ጉዳይ፡** የፍትሐብሔር እና የእምነት ማጉደል ወንጀል ግልፅ ድንበር ማስቀመጥ ባለመቻሉ መነሻቸው የውል ስምምነት የሆኑ ጉዳዮች የፍትሐብሔር ባህሪ ያላቸው ስለመሆኑ በወንጀል ስለሚያስከስሱበት ሁኔታ ብዥታ ያለ ከመሆኑ ባሻገር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 675/3 ላይ እምነት ያጎደለ ሰው ንብረቱን መልሷል ተብሎ መዝገቡ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ ላይ የተለያየ አረዳድ እና ውሳኔ ልዩነት ታይቷል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

አንድን ንብረት በውል ግንኙነት መሰረት በተከሳሽ እጅ ቢገባ የግል ተበዳይ ተከሳሹን በውል መሰረት እንዲፈጽም በፍታብሔር ክርክር ይጠይቀዋል፡፡ ሆኖም ግን በአደራ ምክንያት የተገኘን ንብረት ለታለመለት ዓላማ ባይውል ወይም ዕቃው ወይም ገንዘቡን ሳይመለስ ቢቀር ተከሳሹን በእምነት ማጉደል ወንጀል ነው የሚጠየቀው፡፡ ከዚህ በተመሳሳይም በተከሳሽና በግል ተበዳይ ውል ቢኖርም የውል ስምምነቱን ሙሉ በሙሉ የማይፈታው ሲሆንና ተጠርጣሪው እምነቱን ሳያከብር ቢቀር ድርጊቱን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675/1 ክስ ሊመሰረት ይገባል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርመራ ስራዎች የመምራትና የመቆጣጠር ሃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ እንዲሁም ተከሳሽ የወሰደውን ንብረት እንዲመልስ ተጠይቆ ሲመልስ ወንጀል የመስራት ሃሳብ (intention) አለው ተብሎ የህግ ግምት ስለማይወሰድበት በእምነት ማጉደል ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ጉዳዩ ገና በምርመራ ላይ እያለ ወይም ዓ/ሕግ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተጠርጣሪው የወሰደውን ንብረት ለግል ተበዳይ የመለሰ እንደሆነ በወ/ሕግ 675(3) መሰረት ክሱ ሊዘጋለት ወይም ሊቋረጥለት ይገባል፡፡

## 1.13 የወንጀል ህግ አንቀፅ 675 እና 692 ተፈፃሚ ስለሚሆኑበት አግባብ

**አከራካሪዉ ጉዳይ፡-** በዕምነት ማጉደልና የማታለል ወንጀል የሚደነግጉትን የህግ ድንጋጌዎች በሚመለከት በአንድ ጽ/ቤት ዉስጥ በሚገኙ ባለመያዎች እንዲሁም በምድብ ጽ/ቤት ቤቶች መሀከል ተመሳሳይ በሆኑ የወንጀል መዛግብት ላይ የተለያዩ አንዳንዴም አርስ በራስ የሚጣረሡ ወሳኔዎች መበራከትከ፡፡

**የጠቅላይ ዓቃቤ ህግ አቋም**

ማታለልና የእምነት ማጉደል ወንጀል ልዩነትን ለመረዳት የእያንዳንዳቸዉን ምንነትና ትርጉም በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

እምነት ማለት አምነትን መሰረት በማድረግ በአደራ ሰጪዉ ጠያቂነት ለአደራ ሰጪዉ ወይም ለሰወስተኛ ወገን ጥቅም ሲባል አንድን ንብረት በሚመለከት በአደራ ሰጪዉ ተለይቶ የተገለፀን ነገር ለማከናወን በአደራ ተቀባዩ ፈቃደኝነት ላይ በመመስረት በአደራ ተቀባዩ ላይ ግዴታን የሚጥል ግንኙነት ነዉ ሲሆን ባለ አዳራ ማለት ደግሞ አንድን ነገር ለማከናወን በፈዳደኝነት ሀፊነትን የተቀበለ ሰዉ ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም አምነት ማጉደል ማለት አደራ ተቀባይ የሆነ ሰዉ ወይም ባለአደራ በአደራ ቃል ላይ የተገለፀን የአደራ ስምምነት ግዴታን ወይም በግለሰቦች መሀከል ያለዉን ግንኙነት መሰረት በማድረግ በርትዕ የተጣለበትን የአደራ ግዴታ መጣስ ፣ አለመፈፀም ወይም አለማክበር የሚያመለክት ቃል ነዉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ማታለል ማለት ሶስተኛ ወገን ስለአንድ ነገር የተሳሳተ ግምት እንዲኖረዉ ወይም የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ በማሰብ አንድን ነገር አስመልክቶ የሚደረግ ሀሰተኛ መግለጫ ወይም አሳሳች ድርጊት ማድረግ ነዉ፡፡

ከላይ የእምነት ማጉደልና የማታለል ድርጊትን በሚመለከት ከተሰጡት ትርጉሞች እና ከወንጀል ህጉ ድንጋጌዎችን ለመረዳት እንደሚቻለዉ በሁለቱም የወንጀል ድርጊቶች ግዜ የተበዳዩ አምነት ያለና የወንጀል ፍሬ የሆነዉም ንብረት ወደ ወንጀለኛዉ የሚተላለፈዉ ያለ ወንጀለኛዉ የሀይል ተግባር በግል ተበዳዩ ፍቃድ ቢሆንም ሁለቱ የወንጀል አይነቶች የሚከተሉት መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች አሏቻዉ፡፡

I. **ንብረቱ ከግል ተበዳይ ወደ ወንጀለኛዉ የሚገባበት መንገድ፡-** እምነት ማጉደል ወንጀል በሚፈፀምበት ወቅት የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመበት ንብረት ከወንጀለኛዉ እጅ የሚገባዉ በግልተበዳዩ አነሳሽነት ወይም ጠያቂነት ሲሆን ወንጀለኛዉ ይህ ንብረት እጁ ለማስገባት የሚያከናዉነዉ ምንም አይነት ተግባር የለም፡፡ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የማታለል ወንጀል በሚፈፀምበት ወቅት የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመበት ንብረት ከወንጀለኛዉ እጅ የሚገባዉ በግልተበዳዩ አነሳሽነት ሳይሆን በተከሳሹ በተሰጠ አሳሳች ወይም ሀሰኛ በሆነ መግለጫ ወይም የግል ተበዳዩ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ በሚያደርግ የወንጀልኛዉ ድርጊት(ማድረግንና አላማድረግን፣ መግለፅንና አለመግፅን ያካትታል) ነዉ፡፡

II. **ተበዳዩ የሚኖረዉ እምነት፡-** የእምነት ማጉደል ወንጀል በሚፈፀምበት ግዜ ምናልባት ወንጀለኛዉ የተጣለበትን እምነት ይወጣል ብሎ ከማመኑ ዉጪ የግል ተበዳዩ ንብረቱን ሲሰጥ የተሳሳተ አምነት አለዉ ወይም ተታሏል ወይም የተሳሳተ ግምት ነበረዉ ሊያስብል የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ በማታለል ወንጀል ግዜ ተበዳዩ ንብረቱን በሚያስተላልፍነት ወቅት ስለሆነ ነገር የተሳሳተ እምነት ይኖረዋል ወይም የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ደርሷል ፤ ይህን የተበዳዩ የተሳሳተ እምነት፣ ግምት

ወይም ድምዳሜ ከወንጀለኛዉ ያልተገባ ድርጊት የመነጨ ከመሆኑም ባሻገር ወንጀለኛዉ የወንጀል ንብረቱ ከግል ተበዳዩ ወደ እራሱ እንዲተላለፍ ተጠቅሞበታል፡፡

III. **የመታለል አስፈላጊነት፡-** የማታለል ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት የግል ተበዳዩ የግድ በተከሳሹ ድርጊት መታለል ይኖርበታል ወይም ስለሆነ ነገር የተሳሳተ ግምት ወይም ድምዳሜ ላይ መድረስ ይኖርነታል በእምነት ማጉደል ወንጀል ወቅት ይህ ሲሆን አይገባም፡፡

IV. **የተበዳዩ የእምነት ምንጭ፡-** የእምነት ማጉደል ወንጀል ወቅት የተበዳዩ እምነት የሚመነጨዉ የግል ተበዳይና ተከሳሹ በነበራቸዉ የቀደመ ግንኑነት፣ መግባባት፣ ትዉዉቅና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሲሆን በማታለል ወቅት የግል ተበዳዩ እምነት የሚመነጨዉ በወንጀለኛዉ የማሳሳት ወይም የማታለል ድርጊት ነዉ፡

V. **ንብረቱ ከተከሳሽ እጅ የሚገባበት አላማ** ፡- በእምነት ማጉደል ወንጀል ወቅት ንብረቱ ከተደዳዩ ወደ ወንጀለኛዉ የሚተላለፈዉ ከንብረቱ ጋር በተያያዘ ወንጀለኛዉ በግል ተበዳዩ አመንጪነት በራሱ ተለይቶ የተገለፀን ድርጊት እንዲያከናዉን ሲሆን ምናልባት የጎንዮሽ የኢኮኖሚ ጥቅም ካልሆነ በስተቀር ወንጀለኛዉ በቀጥታ ከንብረቱ የሚያገኘዉ ምንም አይነት ጥቅም የለም፡፡ይልቁንስ ወንጀለኛዉ ንብረቱን መሚመለከት እንዲያከናዉን በተበዳዩ የታዘዘዉ ድርጊት ለተበዳዩ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ሰዉ ጥቅም ነዉ፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረዉ በሁለቱ ወንጀሎች መሀከል ከላይ የተዘረዘሩት ልዩነቶች ያሉ በመሆኑ እነዚህን መስፈርቶች  አንድ ላይ በመጠቀም ወጥነት ያለዉና ተመሳሳይ የሆነ ዉሳኔ መስጠት ይገባል፡፡

## 1.14 በመሸሸግ ወንጀል ተጠርጣሪው ንብረቱ የተገኘው በአንድ ንብረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል ምክንያት መሆኑን እንደሚያውቅ ወይም ማወቅ እያለበት የሸሸገ ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ የሚገባው ስለመሆኑ፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 682

**አከራካሪው ጉዳይ፤-** የመሸሸግን ወንጀል አስመልክቶ 682(1) ….ማንም ሰው እቃው የተገኘው በአንድ ንብረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል ምክንያት መሆኑን እያወቀ ወይም 682(3) መሰረት ተግባሩ በቸልተኝነት ሲፈጸም እቃው የተገኘው በአንድ ንብረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል ምክንት መሆኑን ማወቅ ሲገባው በሚል ስለሚያስቀምጥ ከመሸሸጉ ተግባር ቀድሞ የተፈጸመ ወንጀል ስለመኖሩ የመሸሸጉን ተግባር ከማረጋጥ በተጨማሪ ማስረዳት አለብ ን የሚለው አንደኛው የባለሙያዎች አረዳድ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከመሸሸጉ ወንጀል በፊት የተፈጸመ ወንጀል ስለመኖሩ ማስረዳት ሳይጠበቅብን የመሸሸግ ወንጀል መፈጸሙን ብቻ ማስረዳት በቂ ነው የሚል አቋም መኖሩ ለውሳኔዎች መለያየት ምክንያት ሆኗል፡፡

**የጠቅላይ አቃቤህግ አቋም**

ዐቃቤ ህግ አንድን ተጠርጣሪ በመሸሸግ ወንጀል ለመክሰስ በሚወስንበት ጊዜ ህጉ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው ዕቃው የተገኘው ባንድ ንብረት ላይ በተፈፀመ ወንጀል ምክንያት መሆኑን ተጠርጣሪው ያውቅ ነበር ወይም ማውቅ እየተገባው ሸሽጓል የሚለውን የህጉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሚያስረዳ ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**1.15 የኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 እና 712ን በተመለከተ በአራጣ ምክንያት የተሰጠ ገንዘብ የሌለው ቼክ በወንጀል ላያስጠይቅ ስለሚችልበት ሁኔታ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡** በአራጣ ምክንያት የተሰጠ ቼክ በሂሳቡ ውስጥ ገንዘብ አለመኖሩ ቢረጋገጥም በወንጀል ሊከሰስ አይገባም ሲሉ ሌሎቹ በበኩላቸው ቼክ ለአምጭው የሚከፈል ገንዘብን ተክቶ የሚሰራ ከመሆኑ አንጻር ደረቅ ቼክ የሰጠው በአራጣ ወንጀል ምክንያት ቢሆን እንኳ ክስ ሊመሰረት ይገባል የሚሉ ናቸው፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተቋማዊ አቋም**

የወንጀል ተግባር በሕግ መሰረት የማያስቀጣ ወይም ይቅርታ የሚያሰጥ ካልሆነ በቀር ምንጊዜም የሚያስቀጣ ነው በማለት የዚሁ ሕግ አንቀጽ 58(2) ይጠቅሳል፡፡

ማንኛውም ታስቦ የሚፈጸም ወንጀል በመርህ ደረጃ አስቀጪ ነው፡፡ በንግድ ሕግ መሰረት ለአምጪው ከሚከፈሉ ሰነዶች መካከል አንዱ ቼክ እንደሆነ እና በአንቀጽ 827 እና 830 መሰረትም ቼክ ያለ ቅድመሁኔታ የሚከፈል፣ አስቀድሞ የገንዘብ ሥንቅ ያለው መሆን የሚገባው እና አስቀድሞም ሥንቅ ባይኖረው የቼኩን ዋጋ የማያሳጣው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በአራጣ ወንጀል ተበዳይ የሆነ ሰው በቂ ገንዘብ የሌለው ቼክ የሰጠሁት ለዋስትና፣ ለመተማመኛ ወይም ለመያዣ ነው በሚሉ ምክንያቶች ከተጠያቂነት የማይድን በመሆኑ በአራጣውም ወንጀል ክስ የሚቀርብ ሆኖ ቼክ በሰጠውም ሰው ላይ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 693 በመጥቀስ ክስ ሊቀርብ ይገባል፡፡

ከዚህ መርህ በተለየ ሁኔታ ግን አንድ በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ የሰጠ ሰው የራሱን ወይም የሌላ ሰውን መብት በቅርብ ከሚደርስ ከባድ ከሆነ አደጋ ለማዳን የፈጸመው ድርጊት፣ አደጋውን በሌላ መንገድ ማስወገድ የማይቻል ከሆነና አድራጊው ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ዘዴዎችን የተጠቀመ ከሆነ አይቀጣም፡፡ በዚህ መሰረት አንድ ሰው የፈፀመው ድርጊት ወንጀል ቢሆንም በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የፈፀመው እንደሆነ አይቀጣም፡፡

በአጠቃላይ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ድርጊት እና አራጣ ወንጀሎች ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ በመሆኑ በአንድ ላይ ሊታዩ ይገባል፡፡ በልዩ ሁኔታ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ የተሰጠው/የወጣው በአስገዳጅ ሁኔታ መሆኑ በጥብቅ ተመዝኖ ክስ ያለማቅረብ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል፡፡

## 1.16 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 702/1 በኤጀንሲዎች አማካኝነት በተቀጠሩ የጥበቃ ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆንበት አግባብ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** በወንጀል ሕግ አንቀጽ 702(1) በውል ግዴታ የሌላን ሰው ንብረት ጥቅም በሚል የሚደነግገው በመካከል በኤጀንሲ አማካኝነት የተቀጠሩ የጥበቃ ባለሙያዎችን ለመክሰስ እነዚህ ጥበቆች ለመጠበቅ ውል የገቡት ከኤጀንሲ ጋር ቢሆንም የሚጠብቁት ኤጀንሲው ከተዋዋለው ሌላ ድርጅት ጋር ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች አሰሪያቸው ኤጀንሲው ነው ወይስ የሚጠብቁት ድርጅት፣ ከባለንብረቱ ጋር ቀጥታ የተዋዋሉት ውል በሌለበት እንዴት በ702(1) መሰረት መጠየቅ ይቻላል የሚል የሕግ ጥያቄ ያስነሳል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

በጥበቃው ሰራተኛና በኤጀንሲው መካከል ውል ሲኖር የጥበቃ ሰራተኛው በሌላ ሰው ጥቅም የስራ አመራር ላይ ጉዳት በሚፈጽምበት ጊዜ ጥበቃውን ለድርጅቱ የሚመድብለት ኤጀንሲው ስለሆነ ጥበቃው በወንጀል ሕግ 702/1 የሚጠየቅ ይሆናል፡፡ ይህን ሳይሆን ቀርቶ ጥበቃው ከኤጀንሲው ጋር የስራ ውል ባይኖራቸው ግን ከሚሰራበት ድርጅት በገቡት ውል መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ከዚህ አልፎ የጥበቃው ሰራተኛ ከኤጀንሲውም ሆነ ከሚጠብቀው ድርጅት ጋር የገባው የጽሑፍ ውል በሌለበት ሁኔታም ቢሆን ውል ወይም በቃል ወይም ደግሞ በጽሑፍ ሊደረግ ከመቻሉ አንፃር ተጠያቂ ሊሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ ከአሰሪው ጋር በጽሑፍ የተደረገ ውል ባይኖርም የአሰሪና ሰራተኛ ውል የጸና ይሆናል በማለት የሰራተኛው መብት ጠብቆለታል፡፡ ስለዚህ አዋጁን የሰራተኛውን መብት ሲያከብርለት የኤጀንሲ ሰራተኛ ሆኖ ለድርጅት ወይም ለግል ባለሀብት በጥበቃነት የሚያገለግል ግለሰብ፣ በጥበቃነት እያገለገለ ባለበት ወቅት የባለሀብቱ ወይም የድርጅቱ ንብረት በጥበቃ ሰራተኛው በማወቅ ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ንብረቱ በሚጠፋበት ጊዜ የጥበቃ ሰራተኛው ተጠያቂ መሆን እንደሚገባው የሚያሳይ እንደምታ ያለው ነው፡፡ በተጨማሪም በኢትጵያ የፍታብሔር ሕግ በአንቀጽ 1727 ስርም እንደ አሰሪና ሰራተኛ የመሳሰሉ ውሎች በሌላ ሕግ በጽሑፍ እንዲሆኑ ግዴታ የተጣለባቸው ባለመሆናቸው በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሰረት በማንኛውም አግባብ ሊከናወኑ እንደሚችሉ የሚያመላክት ስለሆነ የጽሑፍ ውል ውል ባይኖርም ግንኙነታቸው ማስረዳት ከተቻለ በጥበቃ ሰራተኛው ላይ በሌላ ሰው ጥቅም የስራ አመራር ለተፈጸመ ጉዳት ክስ ሊመሰረት ይገባል፡፡

**1.17 በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 712(1) ሀ ስር የአራጣ ወንጀል ተፈጽሟል የሚባለው ተበዳሪው የገንዘብ ችግር ያለበት መሆኑ እና አበዳሪው ይህን የተበዳሪውን ችግር በመጠቀም ለተበዳሪው በሕግ ከተፈቀደው ወለድ በላይ ያበደረ ስለመሆኑ በአንድነት (Cumulatively) ሲረጋገጥ ስለመሆኑ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡** የአራጣ ወንጀል ተፈፀመ ለማለት የተለየ የወለድ መጠን የለም የሚል በአንድ በኩል፣ ሌሎች ባለሙያተኞች በፍትሐብሔር ሕግ የተመለከተው የ12 በመቶ የወለድ መጠን ተፈጻሚ በማድረግ ውሳኔ የሚሰጡበት መሆኑ እና አንድ ሰው ሳይቸግረው ብድር አይጠይቅም ሲሉ በተቃራኒው የሚቆሙት መቸገሩንም በተጨማሪ ሲረጋገጥ ብቻ ነው የአራጣ ወንጀል አለ የሚባለው በማለት ለተመሳሳይ ድርጊት የተለያየ ድምዳሜ ላይ የመድረስ ልዩነት ፈጥሯል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተቋማዊ አቋም**

አንድ ሕግ ለትርጉም ተጋልጦ ሲገኝ ሕጉን ተፈጻሚ የሚያደርግ የአተረጓጓም ስልት መከተል የዳበረ የሕግ ባህል ሲሆን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 712(1)ሀ አራጣ ወንጀልን ከሚያቋቁሙ ፍሬነገሮች መካከል አንዱ ከሕጋዊ የወለድ መጠን በላይ አበድሮ መገኘት ሲሆን ይህ የወለድ መጠን በብሔራዊ ባንክ አልተወሰነም በሚል የወንጀል ሕጉን ድንጋጌ ተፈጻሚ እንዳይሆን ማድረግ ተገቢ አይደለም፡፡ ይልቁንም ድንጋጌው ተፈጻሚ የሚሆንበትን የአተረጓጎም ሂደት መከተል የሚገባ በመሆኑ የብሔራዊ ባንክ የወለድ መጠን የመወሰን ስልጣን የፋይናንስ ተቋማትን እና ባንኮችን የሚመለከት እንጂ በግለሰቦች መካከል የሚኖር የብድር ውልን በተመለከተ ገዢ እንዲሆን ታስቦ የወጣ ባለመሆኑ እና የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2479 ስር የተደነገገው የወለድ መጠን(ጣሪያ) በግለሰቦች መካከል ለሚደረግ የወለድ መጠንን በመጠቀም የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 712(1)ሀን ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡

በኢ.ፌ.ድ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 712 ወንጀል ተደርጎ የተቀመጠው ከሕጋዊ ወለድ በላይ ማበደር አይደለም፡፡ በዚህ ድንጋጌ ወንጀል ሆኖ የተቀመጠው የተበዳሪውን ችግረኛ መሆን፣ የበታችነት ወይም የገንዘብ ችግር መሰረት በማድረግ ከህጋዊ ወለድ በላይ ገንዘብ ማበደር ነው፡፡ የእንግሊዘኛው ንባብ whoever, by exploiting …በማለት መጀመሩ እና የአራጣ ወንጀል የሚገኘው በክፍል ሶስት የኀሊናን ወይም የሰውን ችግር መሰረት በማድረግ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ስር ከመሆኑ አንጻር ጥበቃ ሊያደርግላቸው የፈለጋቸው ሰዎች በችግር፣ በልምድ ወይም ችሎታ ማጣት ወዳልተመጣጠነ ግዴታ የሚገቡትን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከአራጣ ወንጀል አንጻር ተበዳዩ ከሕጋዊ ወለድ መጠን በላይ ከመበደሩም በተጨማሪ በወቅቱ የገንዘብ ችግር የነበረበት መሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

### የጦር መሳሪያ ብዛትን፣ የመሽጋገሪያ ድንጋጌን እና ለግል መጠቀሚያ ከውጭ አገር የሚገባን የጦር መሳሪያ አስመልክቶ አዋጅ ቁ. 1177/12 ሊተረጎም ስለሚገባው አግባብ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-**

1. የአዋጁ ትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(2) እና 2(10) የጦር መሳሪያ ጥይትን የሚጨምር ከሆነና ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ ማለት ደግሞ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆነ የጦር መሳሪያ ከሆነ አንድ መሳሪያ እና አንድ ጥይት ወይም ሁለት ፍሬ ጥይት ብቻ ይዞ የተገኘ ሰው ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ ይዟል በሚል በአንቀጽ 23(3) ስር ከብዶ ሊከሰስ ይገባል? ወይስ ጥይት የመሳሪያ/የጠመንጃ/ አክሰሰሪ/ደባል/ እቃ እንደሆነ ተቆጥሮ የጦር መሳሪያ ቁጥር ሊወሰን የሚገባው በመሳሪያው/በጠመንጃው/ የመያዝ አቅም መሆን አለበት?

2. ከአዋጁ መሽጋገሪያ ድንጋጌ አንቀጽ 23(2) ጋር ተያይዞ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ለተቆጣጣሪ ተቋሙ አቅርበው ፈቃድ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉት ተቆጣጣሪ ተቋሙ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መሆኑ ስለተገለጸ በዚህ የ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ተቋሙ የጊዜ ሰሌዳ ሳያወጣ 1 ዓመቱ ስላለፈ የጦር መሳሪያ የያዙት ሰዎች ደግሞ ተቆጣጣሪ አካሉ የሚያወጣውን የጊዜ ሰሌዳ እየጠበቁ ሳያስመዘግቡ ጊዜው ስላለፈ የጦር መሳሪያ ይዘው ሲገኙ በአዋጁ መሰረት በወንጀል ሊጠየቁ ይገባል ወይ?

3. ለግል መጠቀሚያ ከውጭ አገር በህጋዊ መንገድ የጦር መሳሪያ ገዝተው ለኢትዮጵያ አየር መንገድም ይህንኑ አሳውቀው ነገር ግን በኢንባሲ በኩልም ሆነ በቀጥታ ለፈቃድ ሰጪው ወይም ተቆጣጣሪው አካል ሳያሳውቁ ወይም ለማሳወቅ ሂደቱን ሳይጀምሩ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ላይ ሲያዙ በአንድ በኩል በአንቀጽ 4(1) መሰረት ማንም ሰው በፌዴራል ፖሊስ ወይም እሱ ውክልና በሰጠው አካል ፈቃድ ሳይሰጠው የጦር መሳሪያ መያዝ፣ ማስቀመጥ፣ ወደ ሃገር ማስገባት፣ ማዘዋወር፣ ማጓጓዝ...የተከለከለ ተግባር ስለሆነ ሊጠየቁ ይገባል የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) ስር የተዘረዘሩት መስፈርቶች ከተሟሉ የጦር መሳሪያ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችል መሆኑ መደንገጉ እንዲሁም አንድ ሰው በእጁ ላይ ባለ የጦር መሳሪያ ላይ ፈቃድ መጠየቅ የሚችል ከሆነ ፈቃድ ይሰጠኛል በሚል ቅን ልቦና ለአየር መንገዱ አሳውቀው ማጓጓዛቸው ወይም ማስገባታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) መሰረት የሀሳብ ክፍል ስላልተሟላ ሊያስጠይቃቸው አይገባም የሚል መከራከሪያ ይነሳል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

ከጦር መሳሪያ ብዛት ጋር በተያያዘ አንድ ግለሰብ አንድ መሳሪያ እና አንድ ጥይት ይዞ ቢገኝ ይዞት የተገኘው ጥይት አብሮ ለያዘው ጦር መሳሪያ አገልግሎት የሚውል መሰል ጥይት ከሆነ

የተጠርጣሪው የሀሳብ ክፍል የሚያሳየው አንድ የጦር መሳሪያ እንደያዘ በመቁጠር ጥቅም ላይ ለማዋል የያዘው መሆኑን ስለሆነ ከብዶ ሊከሰስ አይገባውም፡፡ አንድ ግለሰብ አንድ ጠመንጃ ከነመሰል ካርታው እና ጥይቱ ይዞ ቢገኝ ጠመንጃውን ለብቻ፣ ካርታውን ለብቻ፣ በካርታው ውስጥ ያለውን ጥይት አውጥቶ ለብቻ በአጠቃላይ የመሳሪያውን አካል በመፍታት ለብቻ ቆጥረን ክስ የምናቀርብ ከሆነ ከግለሰቡ የሀሳብ ክፍል በላይ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ጥይቱን ብቻውን ይዞ ቢገኝ ከተጠያቂነት አያድንም፡፡ ምክንያቱም የያዘውን ጥይት ከመሰል ጦር መሳሪያ ወስዶ ገጥሞ ጥቅም ላይ ሊያውለው ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ለማድረግ ማሰቡን ስለሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ሁለት ፍሬ ጥይት ብቻ ይዞ ቢገኝ ሁለቱም ፍሬ ጥይቶች ለተመሳሳይ ጦር መሳሪያ የሚያገለግሉ ከሆኑ እንደ አንድ ጥይት የሚቆጠር ሲሆን ለተለያየ ጦር መሳሪያ የሚያገለግሉ ከሆነ ግን ከጥይቶቹ ጀርባ ያለውን የተለያየ ጦር መሳሪያና ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ከብዶ ሊከሰስ ይገባል፡፡

የአዋጁን አንቀጽ 23(2) በተመለከተ በዚህ ድንጋጌ የሚሸፈነው አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎችን ነው፡፡ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት መሳሪያው በእጃቸው የገባ መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 23(2) ስር ተቆጣጣሪው ተቋም ‹‹በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት›› በእንግሊዘኛው ትርጓሜ ‹‹as per the schedule that it announces›› በሚል የተደነገገው መሳሪያ የሚመዘገብበትን የጊዜ ሰሌዳ ተቋሙ ማሳወቅ የሚገባው መሆኑንና ተቋሙ በሚያሳውቀው ጊዜ መሰረት ቀርበው ማስመዝገብ የሚገባቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም አዋጁ በሚደነግገው መሰረት የሚወጣውን የጊዜ ሰሌዳ በመጠባበቅ ላይ እያሉ ተቋሙ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት ጊዜው ካለፈ ግለሰቦቹ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ነበራቸው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ሆኖም ግን የጦር መሳሪያውን የያዙት ወይም በእጃቸው የገባው አዋጁ ከጸና በኋላ መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ በአዋጁ አንቀጽ 23(2) የሚሸፈን ስላልሆነ ማስረጃው ተመርምሮ ሊከሰሱ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የተደነገገው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የጦር መሳሪያው በእጃቸው ገብቶ ነገር ግን በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ያላስመዘገቡ ከሆነ የሚወረስ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ አዋጁ ከጸና በኋላ ማንም ሰው ፈቃድ ሳያገኝ የጦር መሳሪያ በእጁ ማስገባት ስለሌበት በዚህ ድንጋጌ ስር የሚሸፈን አይደለም፡፡

ከውጭ አገር የሚገባ የጦር መሳሪያን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 4(1) ስር ማንኛውም ሰው የጸና ፈቃድ ሳይኖረው የጦር መሳሪያ ወደ ሃገር ማስገባት እንደማይቻል ህጉ በግልጽ/strict liability/ ያስቀመጠ ስለሆነ መሳሪያው ከመጣበት(ከተጫነበት) አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አሳውቆ መጫኑ ወይም ደክሌር ማድረጉ ዕቃን ከመጫንና ከታክስ ጋር የተያያዘ ስራ እንጂ ህጋዊ

የማድረግ ሂደት ከመጀመር ጋር የተያያዘ አይደለም አየር መንገዱም ቢሆን እንዲህ አይነት ስልጣን የለውም፡፡ በመሆኑም የጦር መሳሪያ የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ከማህበረሰቡ ሰላምና ደህንነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ከወንጀሉ ባህሪ አንጻር መሳሪያውን ለመጫን ሂደቱን ከአየር መንገዱ ጋር ከመጨረስ ባለፈ የማስመዝገብ ወይም የማስፈቀድ ሀሳብ ቢኖረው ኖሮ ቀድሞ እዚያው መሳሪያውን ከገዛበት ወይም እቃውን ከጫነበት አገር ከሚገኝ የኢትዮጵያ ኢንባሲ ወይም ቆንስላ በኩል ወይም በሌላ ህጋዊ መንገድ በተቆጣጣሪ ተቋሙ በኩል ሂደቱን ስለመጀመር አለመጀመሩ ወይም የማሳወቅ ስራ ስለመስራቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ድርጊቱ በህግ የተከለከለ መሆኑን እያወቀ የሆነው ይሁን በሚል/indirect intention/ ውጤቱን በመቀበል ድርጊቱን መፈጸሙን የሚያሳይ ነው፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**ከኢኮኖሚ ነክ የወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የአተረጓጎም ልዩነት የፈጠሩ ድንጋጌዎችና በጉዳዮቹ ላይ የጠቅላይ አቃቤ ሕግ አቋም**

**2.1. የንግድ ውድድር እና ሸማቾች መብት ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/06 አንቀጽ 24/1 እና 43 የተፈጻሚነት ሁኔታ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡** በተመሳሳይ ድርጊት ረገድ አንዳንድ ባለሙያ ክስ የሚያቀርብ ሲሆን ሌላው ደግሞ ክስ አያስመሰርትም በሚል መዛግብት ላይ ውሳኔ እየተሰጠ የሚገኝ እንዲሁም ፍ/ቤቶችም አብዛኞቹን ክሶች ውድቅ የሚያደርጉበት እንዲሁም አንዳንድ ፍ/ቤቶች(ዳኞች) ደግሞ ቅጣት የሚወስኑባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው በዜጎች በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብታቸው እየተጣበበ በመሄዱ የፍትሕ ስርዓቱ ላይ አመኔታ ማጣት ማስከተሉ ተስተውሏል፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

አንቀጽ 24(1) በገበያ ላይ እጥረት ያለበት መሆኑ በሚስቴሩ በወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸን የንግድ ዕቃን፡-

1. ማንኛውም ነጋዴ ከመደበኛ የግብይት አሰራር ውጪ ወይም
2. ነጋዴ ላልሆነ ሰው ለግል ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚል መጠን በላይ ማከማቸት ወይም መደበቅ አይቻልም በማለት የዚህን ድንጋጌ በመተላለፍ የንግድ ዕቃዎችን አከማችቶ ወይም ደብቆ ወይም በሕገወጥ መንገድ ሲያጓጉዝ የተገኘ ማንኛውም ነጋዴ በወንጀል እንደሚቀጣ በአንቀጽ 43(4) ስር ተደንግጓል፡፡

ከዚህም በመነሳት አንድ ተከሳሽ ይህን ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሊከሰስ የሚችለው ተከታዮቹ ነጥቦች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡

- የንግድ ዕቃውን በተመለከተ ንግድ ሚኒስቴር በገበያ ላይ እጥረት ያለበት መሆኑን በሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸ እና
- ነጋዴው ይህንኑ ዕቃ ከመደበኛ የግብይት አሰራር ውጪ ያከማቸ ወይም የደበቀ ወይም ያጓጓዘ፤ ወይም
- ነጋዴ ያልሆነ ከግል ወይም ከቤተሰብ ፍጆታ ከሚል መጠን በላይ ያከማቸ ወይም የደበቀ ወይም ያጓጓዘ እንደሆነ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር አንዱ ማቋቋሚያ ፍሬነገር በንግድ ሚኒስቴር በገበያ ላይ እጥረት ያለበት ዕቃ ስለመሆኑ በሕዝብ ማስታወቂያ መገለጹ ነው፡፡ ምንም እንኳ አሁን ላይ በስራ ላይ ያሉ

አንዳንድ መመሪያዎች እና ማስታወቂያዎች በግልጽ በሚኒስቴሩ ባይወጡም የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097 አንቀጽ 10(6) የንግድ ሚኒስቴር ከተሰጡት ስልጣናት መካከል ለአዲስ አበባ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ በሚሰጠው ውክልና የሚወጡ መመሪያዎች በራሱ በሚኒስቴሩ እንደወጡ የሚቆጠሩ ቢሆኑም ዋነኛው ነጥብ በስራ ላይ ያሉት መመሪያዎች እና ሕዝብ ማስታወቂያዎች ከላይ በተጠቀሰው አግባብ በገበያ ላይ እጥረት ያለበት ዕቃ ስለመሆኑ በሕዝብ ማስታወቂያ ተገልጿል ወይ የሚለው መታየት አለበት፡፡ በንግድ ሚኒስቴር በ2008 የመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎችን ለህብረተሰቡ ለማሰራጨት የወጣውን መመሪያ ስንመለከት የሚዳስሰው ስለመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎች ስርጭት እንጂ በገበያ ላይ እጥረት ስላለባቸው ዕቃዎች አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ መመሪያው የሚያገለግለው ለየአዋጅ ቁጥር 813/06 የመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ዋጋ ስለመወሰን እና ስርጭት የሚደነግጉት አንቀጽ 25 እና 26 ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ የዚህንም ሆነ ይህን መመሪያ መሰረት ተደርገው በከተማ አስተዳደሩ የወጡ መመሪያዎች እንዲሁም በሚኒስቴሩ የወጡ የህዝብ ማስታዊያዎች የሚዳስሱት መሰረታዊ የንግድ ዕቃዎችን ከመሆኑ አንጻር በአዋጁ አንቀጽ 24 ከአንቀጽ 43(4)(5) ጋር በተጣምሮ የሚያስከስስ ሳይሆን በአንቀጽ 43(6) መሰረት አዋጁን ተከትሎ የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን ወይም ሕዝባዊ ማስታወቂያዎችን በመጣስ የሚፈጸም ድርጊት የሚያስቀጣ በመሆኑ በዚሁ አግባብ ክስ ሊቀርብ የሚገባ ሲሆን ከዚህ በመለስ ባሉ ጉዳዮች ረገድም ቢሆን ግልጽ የሆነ በገበያ ላይ እጥረት ያለባቸው ዕቃዎች መሆኑ በግልጽ ከተመለከተ እና የስርጭት ስርዓታቸው በውል የተዘረጋላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከተገኘ ብቻ በአዋጁ አንቀጽ 24(1) እና 43(4)(5)ን በመጥቀስ ክስ ማቅረብ ይገባል፡፡

### 2.2. የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 (በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻለው) እና የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ሕግጋት ላይ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችን የሚመራ ስራ አስኪያጅ በመሆን ብቻ በወንጀል የሚጠየቅበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ፡** ከፊሉ ባለሙያ የድርጅት መሪዎችን ሲከስ ከፊሉ ደግሞ ባለመክሰስ የወንጀል ሕግን ለሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጸማል የሚለውን የዜጎች እኩልነት መርህ የሚጋጭ የሕግ አፈጻጸም መኖሩ ነው፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ከሕግ አውጭው አሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ሕጉ በድርጅቶችም ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በማሰብ ቢሆንም የንግድ ድርጅቶች ኃላፊዎች ሊጠየቁ እንደሚችሉ ግን የተለየ የሚያስቀምጠው ወይም የሚያመለክተው ድንጋጌ የለም፡፡

የወንጀል ህግ አንቀፅ 34 በድርጅት ላይ ክስ ሊቀርብ እንደሚችል የደነገገ ሲሆን፤ክስ የሚቀርበውም ከድርጅቱ ሰራተኞች ወይም ኃላፊዎች አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያያዘ የድርጅቱን ጥቅም በህገ-ወጥ መንገድ ለማስጠበቅ በማሰብ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ነው፡፡

በሁለቱ አዋጆች ረገድ የድርጅቶቹ ኃላፊዎች ወይም ስራ አስኪያጆች በቀጥታ የጉሙሩክ ሕጉን ወይም የንግድ ውድድር እና የሸማቾች አዋጆችን ጥሰው ወንጀል የፈጸሙ አሊያም በትዕዛዝ፣ በመርዳት፣ በመምከር ወይም በሌላ በወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍል በተመለከቱ የወንጀል ተሳትፎዎች መስፈርት ተሳትፎ ካልተገኘ በስተቀር የድርጅቱ መሪ ነው በሚል ብቻ በነዚህ ሕጎች ስር በተጠቀሱ የወንጀል ድንጋጌዎች ክስ ሊቀርብ አይገባም፡፡

## 2.3. በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ተወካይ እና የባለቤት/የግለሰብ ነጋዴ/ ተወካይ የወንጀል ተጠያቂነት ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ፡** በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የወከለው ሌላ ሰው (ተወካይ) እና የባለቤት/የግለሰብ ነጋዴ/ ተወካይ በሚመለከት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ አግባብ በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑ እንደዚሁም በአዋጁ ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ውስጥ ለተፈጸመ ጥፋት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ድርጊት ተሳትፎ ያለመኖሩን እና ከእውቀቱ ውጪ የተፈፀመ መሆኑ በምርመራ ሲረጋገጥ አቃቤ ህግ መዝገቡ መዝጋት አለበት ወይስ ፍ/ቤት እንዲወስን ክስ ማቅረብ ይገባል በሚለው ላይ ህጉ ግልጽ ስላልሆነ አቃቤያነ ህግ መዝገብ ላይ የተለያየ ውሳኔ ከመስጠታቸው አንፃር በዜጎች መካከል ልዩነት የሚፈጥርና የእኩልነት መርህን ያልተከተለ ነው፡፡

### የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም

የታክስ ወንጀል በዋናነት የሚፈፀመው በታክስ ከፋዮች ሲሆን በሌላ ሁኔታ ማንኛውም ሰው በታክስ ወንጀል ተግባር ላይ በወንጀል ህግ አንቀጽ 33 በተደነገገው መሰረት በልዩ ወንጀል ተካፋይ በመሆን እንደ ዋና ወንጀል አድራጊ በመሆን ወይም እንደ አባሪ ሊሳተፍ እንደሚችል ከታክስ አስተዳደር አዋጅ 116/1 እና 128 ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡

ከንግድ እንቅስቃሴው ጋር በተገናኘ በሁሉም መመዘኛ ሲመዘን በወካዩ ደረጃ ላለ ሰው ውክልና ሰጥቶና ተወካዩ በነፃነት ሥራው እየመራና እየተቆጣጠረ ባለበት እንደዚሁም ወካይ የንግድ ሥራው ላይ እየተሳተፈ ባልሆነበት ሁኔታ በተፈፀመ ወንጀል እንዲጠየቅ ማድረግ የንግዱ ማህበረሰብ ተጠያቂነት ይመጣብኛል በሚል ፈሪ የሚያደርግ፣ታክስ ካፋይ ራሱ በአካል መስራት የማይችልባቸው የንግድ ሥራዎች ላይ ያለመሳተፍ በዚህም የንግድ ሥራዎች በጥቂቶች ብቻ ተወስኖ የሚያስቀር ውጤት የሚያስከትልና መንግስት መሰብሰብ ያለበትን የታክስ ገቢ ላይ ተጽእኖ መፍጠር የሚሉት ጉዳቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ስለዚህ የተሟላ ውክልና የሰጠ ወካይ በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ተወካዩን መክሰስ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ አግባብ ተጠያቂ የሚሆን ተወይ ለወካይ የረዳ በሚል በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 128 ሥር ሳይሆን በወንጀል ህግ አንቀፅ 33 እና የታክስ አስተዳደር አዋጁ ላይ ባሉት ሌሎች አንቀፆ ሥር መሆን ይገባዋል፡፡ ታክስ ከፋይ (ግለሰብ ነጋዴ) ወይም የድርጅት ሥራ አስኪያጅ ይህንን ግዴታ በመተላለፍ/ባለመፈፀም በወንጀል ተከሶ እንደሆነ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ሊሆን የሚችሉት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 132(2)(ሀናለ) ላይ በተመለከተው አግባብ ሳያውቁት ወይም ሳይፈልጉት እንደዚሁም ተገቢውን የአሰራር ስርዓት ዘርግተው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

ዐቃቤ ህግ የተጣራውን መዝገብ ሲቀርብለት የንግድ ድርጅቱ ውስጥ የተፈፀመው ጥፋት ስራ-አስኪያጁ ወይም ግለሰብ ነጋዴው ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ ወይም አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብለው የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን፣ተገቢውን ትጋት ወይም የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ መወሰዳቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች የምርመራ መዝገቡ ውስጥ ከቀረቡና በፍ/ቤት ጥፋተኛ የማያሰኛቸው መሆኑን ከወዲሁ አቃቤ ህጉ ከተረዳ  ክስ ማቅረብ ተገቢነት የሌለውና ህግን መሰረት ያላደረገ ስለሚሆን አቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡን ሊዘጋው ይገባል፡፡

## 2.4. የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 118 እስከ 122 እና 125 የሚፈጸሙበት ሁኔታ

**አከራካሪው ጉዳይ፡** በየአንዳንዱ ድንጋጌ ክስ ይቀርባል ወይስ ድርጊቶቹን አጠቃሎ በሚይዘው በታክስ (ግብር ስወራ) ወንጀል ብቻን በሚደነግገው አንቀጽ ስር በአንድ ክስ ይቀርባል የሚለው ዋነኛው ነጥብ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ በአዋጁ አንቀጽ 118 እስከ 122 ድረስ ያሉት ተግባራት አንደኛው በአንደኛው የመሸፈን(የመዋዋጥ) ወይም አሻሚ የመሆን ክፍተት መኖር የሚለው ነው፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

አከራካሪ የሆኑት ነጥቦች ላይ የሕግ መውጣቱ አስፈላጊነት፣ የሕጉ ዓላማ፣ የሕግ አውጭን አሳብ እና ለተፈጻሚነት የሚያመቸውን የትርጉም አካሄድ በመከተል አንቀጽ 118 ተፈጻሚነት ለገቢ ሰብሳቢው አካል ወይም ባለሥልጣን አስቦ ወይም በከባድ ቸልተኛነት ሀሰተኛ(ያልሆነን ነገር እንደሆነ ወይም የሆነውን ነገር እንዳልሆነ አድርጎ በመግለጽ ከእውነታው ወይም ከታወቀው ፍሬነገር ጋር የሚቃረን) መግለጫ መስጠትን ወይም መግለጫው ከሚቀርብላቸው ሰዎች መካከል አንዱን በምክንያታዊነት ሲታይ ሊያሳስት የሚችል ሆኖ ሲገኝ ወይም ሲታመን ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን ሌላኛው ሁኔታ የተጭበረበሩ ሰነዶችን ለባለስልጣኑ ማቅረብ ሲሆን በዚህም ረገድ የሰነዶቹን ባህሪ፣ ይዘት፣ ሁኔታ የቀየረ ወይም ወደ ሀሰት የቀየረን ሰው ሊመለከት የሚችል ማንኛውም ሰነዱን ያቀረበ ሰው የሰነዱ መጭበርበር ከመረጋገጡ በተጨማሪነት ሰነዱን ያቀረበው አስቦ ወይም በከባድ ቸልተኝነት መሆኑ መረጋገጥ ሲችል ዐቃቤ ሕግ ክሱን ሊመሰርት የሚገባ ሲሆን በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ስርም የተደነገጉት ከዚሁ ጋር ተጣጥመው ሊፈጸሙ የሚገቡ ናቸው፡፡

አንቀጽ 119ን በተመለከተ ማንኛውም ሰው የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠ ወይም ያሰራጨ፤ ወይም የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ ወይም ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የሚያስቀጣው በቸልተኝነት ሳይሆን ታስቦ ሲፈጸም ብቻ ነው፡፡ ተከሳሽ የሚሆነው አካል ስለ ደረሰኞቹ ሀሰተኛነት አውቆ የሚያስከትለውንም ውጤት ተቀብሎ አሊያም የሆነው ይሁን ብሎ የፈጸመው መሆን ይገባዋል፡፡

በአንቀጽ 120 ስር ያለ ፈቃድ ደረሰኝ ማተምን የከለከለ ሲሆን ፈቃድ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ወንጀልነቱ ሊቀር የሚችል ሲሆን በአንቀጽ 119(1) ስር መሸፈን የተፈለገው የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ማዘጋጀት ሲሆን የሁለቱ ድንጋጌዎች እንግሊዝኛ ትርጉም ይኼንኑ ግልጽ የሚያደርግ ነው፡ A person who: prepares, ***produces***, sells, or distributes fraudulent invoices; የሚል ሲሆን አንቀጽ 120(6) ግን 'Whosoever without authorization from the Authority ***prints*** tax invoices…' በሚል ያስቀመጠው ከመሆኑ አንጻር የአንቀጽ 119(1) 'ያሳተመ' የሚለው 'የፈጠረ' በሚል አንደምታ ሊታይ የሚችል በመሆኑ ዐቃቤ ሕግም በነዚህ መስፈርቶች መሰረት ተገቢውን ድንጋጌ ከቀረቡ ማስረጃዎች እና ከነገሮች ሁኔታ በመተርጎም ክስ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

ሌላኛው በአዲሱ አዋጅ 983/08 ውስጥ ለብቻው አንድ ድንጋጌ ሆኖ የተካተተው ሕገወጥ የሆነ ተመላሽን ወይም ከተገቢው በላይ ማካካሻን መጠየቅ የሚለው ድርጊት ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 285/94 በአንቀጽ 49 ስር በግብር ስወራ ውስጥ ተካቶ የነበረ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በዚሁ መሰረት አዲሱ የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 121 ባለሥልጣኑን ለማጭበርበር በማሰብ ተመላሽ ወይም ማካካሻ መጠየቅን አስቀጪ ተግባር አድርጎታል፡፡

በዚሁ ሕግ አንቀጽ 125 መሰረት የታክስ ስወራ ወንጀል ጋር ተያይዞ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስን የመሰብሰብ ግዴታ እያለበት ባለመሰብሰቡ ብቻ አንድ ሰው የግብር ስወራ ወንጀል ፈጽመሃል ተብሎ ሊከሰስ የሚችልበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ሆኖም ግን እንደየሁኔታዎቹ አግባብነት እና እንደተጠናቀሩት ማስረጃዎች ይዘት ያለ ደረሰኝ ግብይት በመፈጸም እና/ወይም ታክስ ለመሰወር በማሰብ ያገኘውን ገቢ ሳያስታውቅ ቀርቶ እንደሆነ በግብር ስወራ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

ከላይ የየድንጋጌዎቹን ይዘት በመመልከት መቼ እና በምን ዓይነት ፍሬነገሮች ረገድ መጠቀስ ይገባቸዋል የሚለው የተዳሰሰ ሲሆን በአንድ ድርጊት እነዚህን ድንጋጌዎች ጥሶ የተገኘስ ስንት ክስ ይቀርብበታል የሚለውን መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 116/2 መሰረት የተለያዩ የታክስ ሕጎችን በመተላለፍ በዚህ ምዕራፍ ስር የተደነገገ ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ እያንዳንዱን የታክስ ሕግ በመተላለፍ እንደተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ተቆጥሮ ለእያንዳንዱ ድርጊት በአንቀጾቹ ላይ የተመለከቱትን ቅጣት ይቀጣል፡፡

አከራካሪ የሆኑት ድንጋጌዎችን በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ከአቀራረጻቸው፣ ከታለሙለት ዓላማ፣ ከሕግ አውጭው አሳብ በመነሳት ዐቃቤ ሕግ በቀጣይ ውሳኔዎቹ በሚከተለው መልኩ ሕጉን መተርጎም እና ማስፈጸም ይገባዋል፡፡

ከላይ የተገለጹት ሁለቱም የሕግ ድንጋጌዎች የየራሳቸው ዓላማ ያላቸው እና በሕግ አውጭውም ሊያሳኩት የታለመላቸው ዓላማ እንዳለ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም በሁለቱም የሕግ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱ ፍሬነገሮችን በማስረጃ የማስደገፍ ሁኔታን ከግምት በማስገባት እንደ ጉዳዩ አግባብነት ለየብቻ ወይም በተደራቢነት ክስ ሊቀርብ እንደሚገባ ግልፅ ነው፡፡ ምክንያቱም የእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መደራረብ የሚከሰተው ከወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) ከተቀመጠው መርህ አኳያ ነው፡፡ ምክንያቱም የታክስ አስተዳደር አዋጁም ሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የገቢ ግብር አዋጆች ሊያሳኩ ካስቀመጧቸው ዋነኛ ግቦች መካከል ሁለቱ የግብር መሰረቱን ማስፋት እና በሰነድ የተደራጀ የግብር መረጃን መዘርጋት ነው፡፡ ከዚህም አንጻር የግብር ስወራ ወንጀል የታክስ መሰረቱን በተሳካ ሁኔታ በማስፈጸም ግብር ከፋዩ የግብር ግዴታውን እንዲወጣ በማስቻል የሀገሪቷ ከግብር የሚገኝ ገቢን ከፍ ባለ ደረጃ መከወን ሲሆን የሀሰት ወይም አሳሳች መግለጫ ማቅረብ ወንጀል በበኩሉ የታክስ ስርዓቱ መረጃ ላይ የተመሰረተ(የሰነድ አጠቃቀም ባህልን ከፍ ያለ) እንዲሆን ለማስቻል ከመሆኑ አንጻር ሁለቱም ድንጋጌዎች በተደራራቢነት መከሰስ ይገባቸዋል፡፡

ሆኖም ግን ሀሰተኛ ደረሰኝ በማቅረብ ግብር ሰውሯል የተባለ ተከሳሽ በዚሁ ድርጊት መነሻ ብቻ የሀሰት ወይም አሳሳች መግለጫ በማቅረብ መከሰስ አይባውም፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ማቅረብ እና ሀሰተኛ ደረሰኝ የማቅረብ ድርጊቶች ተመሳሳይ ዓላማ

ያላቸው እና በአንድ ወንጀል በማድረግ አሳብ የሚፈጸሙ ተመሳሳይ ግብን በሚያሳኩ ድንጋጌዎች ስር ስለሚሸፈን ይኼንኑ ያገናዘበ ክስ ሊቀርብ ይገባል፡፡

## 2.5. የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀፅ 120 (1) እና አንቀፅ 131 (1(ለ)) የተፈፃሚነት አግባብ

**አከራካሪዉ ጉዳይ፡-** የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983 አንቀፅ 120 (1) እና አንቀፅ 131 (1ለ) በምን አግባብ ነው ክስ ላይ መጠቀስ ያለባቸው የሚለው ጉዳይ ለውሳኔዎች መለያየት ምክንያት መሆን

**የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

በህግ በተጣለባቸዉ ግዴታ ወይም በፍቃዳቸዉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ወስደው ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች (ከንግድ ሥራው ባህርይ የተነሳ በልዩ ሁኔታ መሳሪያው መጠቀም የማይገደዱትን ሳይጨምር) ለሚያከናውኑት ግብይት በምን ሁኔታ ላይ ሲገኙ ነው የማንዋል ደረሰኝ መስጠት ያለባቸው የሚለውን ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ወስደው መሳሪያውን ለመጠቀም የሚከለክል በአዋጅ 983/08 አንቀፅ 131(1ለ) የተገለፁት አስገዳጅ ሁኔታዎች እስከሌሉ ድረስ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የታተመ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 113 (1)፣131 (1ለ) እና የደረሰኝ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 149/2011 አንቀጽ 9 (1) ጣምራ ንባብ መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ስራ ላይ እያለ ደረሰኝ ላለመስጠት የሚያበቁ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሳይከሰቱ የማንዋል ደረሰኝ መቁረጥ ክልክል መሆኑ ስለሚያሳዩ የሽያጭ መሳሪያዉ በስራ ላይ እያለ እንደ አማራጭ የማንዋል ደረሰኝ የቆረጠ ግብር ከፋይ በአንቀጽ 131 (1ለ) መሰረት ተጠያቂ መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ለመጠቀም የማያስችሉ ማለትም በአንቀጽ 131 (1ለ) ስር የተገለፁት አስገዳጅ ሁኔታዎች ከተከሰቱ ግብር ከፋዩ መስጠት የሚጠበቅበት የደረሰኝ አይነት የማንዋል ደረሰኝ በመሆኑ ይህን የማንዋል ደረሰኝ ካልሰጠ በዚሁ አንቀፅ 131 (1ለ) መሰረት ተጠያቂ መደረግ እንዳለበት ከላይ ከተገለፀት የህጉ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የሽያጭ መመዝገቢ መሣሪያው ሥራ ላይ ባለበትና ለመጠቀም የሚከለክሉ በህጉ አንቀፅ 131 (1ለ) የተዘረዘሩት አስገዳጅ ሁኔታዎች በሌሉበት ሁኔታ ከሁለቱ የደረሰኝ አይነቶች የትኛውንም አይነት ደረሰኝ ካልቆረጠ ከሁለቱ አይነት ደረሰኞች አንዱንም አለመስጠቱ ሲታይ ግብር ከፋዩ ደረሰኝ የመስጠት ፍላጎት የሌለው መሆኑንና የሀሳብ ክፍሉም በጠቅላላው ደረሰኝ አለመስጠት መሆኑ ግልጽ አድርጎ ስለሚያሳይ ድርጊቱ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ጋር በተገናኘ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች በመውጣት ከደረሰኝ ጋር የተገኛኙ ጠቅላላ ወንጀሎች የሚደነግገው አንቀጽ 120 (1) ሥር ክስ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## ከሙስና ወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የአተረጓጎም ልዩነት የፈጠሩ ድንጋጌዎችና በጉዳዮቹ ላይ የጠቅላይ አቃቤ ሕግ አቋም

### 3.1 በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደ ህዝባዊ ድርጅት ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመሰራረቱ ከህዝብ በሚሰበሰብ ገንዘብ አይደለም የሚቋቋመው የሚል እሳቤ በመኖሩ መነሻነት ህዝባዊ ድርጅት ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ጉዳይ እንዲሁም የግል ድርጅቶችን በተመለከተ በሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ህዝባዊ ድርጅቶችን በአባልነት በመያዝ የተመሰረተ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደ ህዝባዊ ድርጅት የሚቆጠር ነውን? በሚሉ ጉዳዮች ላይ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ግልፅ ባለመሆኑ ምክንያት ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደ ህዝባዊ ድርጅት ተቆጥሮ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ይሸፈናል አይሸፈንም የሚለው ዋና ፍሬ ነገር ነው፡፡

**የጠቅላይ አቃቤ ህግ አቋም**

ቀድሞ በመንግስት ሰራተኞችና በመንግስት መስሪያ ቤቶች ጥቅም ላይ ብቻ የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች ለመከላከል ስራ ላይ የነበረውን ህግ በመተካት የወጣው አዲሱ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ የግል ዘርፉን በማካተት የመጣው አለምአቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶች በሀገሪቱ ላይ የጣሉትን ግዴታ ለመወጣት ጭምር መሆኑን በመግቢያው ላይ ገልፆታል፡፡

ኢትዮጵያ ፈርማ በማፅደቅ የሀገራችን የህግ አካል ያደረገቻቸውና በተባበሩት መንግስታት ደረጃም ሆነ በአፍሪካ ሀገራት መካከል ሙስናን ለመዋጋት የተፈረሙ ስምምነቶች በፈራሚ አገራት ላይ የሚጥሉት ግዴታ ደግሞ በግል ዘርፉ ላይ የሚፈፀሙ የጉቦኝነት እና የምዝበራ ድርጊቶችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው የህግና የአሰራር እርምጃዎችን እንዲወስዱ የሚል ሲሆን የትኛውን የግል ዘርፍ በሚለው ጉዳይ ላይ ግን ለይቶ ያስቀመጠው ነገር ባለመኖሩ የግል ዘርፍ ውስጥ ስለሚካተቱና ከዝርዘሩ ውጭ ስለሚሆኑ ድርጅቶች ጉዳይ ውሳኔ መስጠትን በተመለከተ ለሀገራት ሉዓላዊ ስልጣን ተላልፎ የተሰጠ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከሙስና አዋጁ አጠቃላይ ይዘት፤ የህግ አውጭውን ሀሳብን ይህንኑ ከሚያረጋግጠው ማብራሪያ፤ ከትርጉም ድንጋጌዎችና በአዋጁ ከትርጉም ውጭ የተደረጉ ዝርዝሮች በመነሳት ሀላፊነቱ ተወሰነ የግል ማሕበር በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር በመርህ ደረጃ የማይካተት መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት የግል ማህበሩ አግባብነት ያለው ኩባንያ የተባለውን ትርጉም የሚያሟላ ሲሆን ማለትም ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር የሚያቋቁመው የሽርክና ኩባንያን የሚያጠቃልል ነው በተባለው

አግባብ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አግባብነት ያለው ኩባንያ ለመሆን የሚችል ሲሆን ብቻ ይካተታል፡፡

## 3.2 ከባድ የሙስና ወንጀል ብሎ ክስ ለማቅረብ የተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ታሳቢ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ:- አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9 (2)

**አከራካሪዉ ጉዳይ፡-** በድንጋጌዉ ለተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ግልፅ መስፈርት ባለመቀመጡ በተመሳሳይ ጉዳይ አንዳንድ ዐቃበያነ ህግ በንዑስ አንቀፅ 1 ክስ ሲያቀርቡ ሌሎች ደግሞ በንዑስ አንቀፅ 2 ክስ የሚያቀርቡበት ሁኔታ መኖር በዚህም የተነሳ በተከሳሾች መካከል የፍትሐዊነት ጥያቄ እያስነሳ መሆኑ፡፡

**የጠቅላይ አቃቤህግ አቋም**

በአዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀፅ 2(9) መሰረት ‹‹ከባድ የሙስና ወንጀል›› ማለት በሰጠዉ ማብራሪያ እና በተሻሻለዉ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀፅ 11(5) መሰረት ለድንጋጌዉ ወጥ አፈፃፀም ይረዳ ዘንድ ወንጀሉ የተፈፀመበት ዓላማ ከባድ የሚያስብል ሆኖ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች መካከል አንዱ ላይ ሲያርፍ ዐ/ህግ ክሱን በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9(2) መሰረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ነዉ ብሎ ለመዉሰድ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺ አንድ) በላይ የሆነ ጉዳት ወይም የተገኘ ጥቅም መኖሩ ሲረጋገጥ ዐ/ህግ ክሱን በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9(2) መሰረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

የተከሳሽ የኃላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ለመወሰን ፍርድ ቤቶች ለቅጣት አወሳሰን የሚጠቀሙበትን መመሪያ በተመሳሳይ በመዉሰድ ክስ ማቅረብ ያለባቸዉ ሲሆን የህዝባዊ ድርጅቶችን በተመለከተ የሚገዙት በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ መሰረት ስለሆነ የስራ መሪዎቻቸዉ ተጠርጥረዉ/ተከሰዉ/ ሲቀርቡ የኃላፊነት ደረጃቸዉ ከፍተኛ የሚባል በመሆኑ ዐ/ህግ ክሱን በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9(2) መሰረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

## 3.3 አጃቢ ፖሊሶች በሚያጅቧቸው እስረኞች ላይ የሚፈፅሙትን ድብደባ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ሳይሆን በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ክስ ማቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** እስረኞችን የሚያጅቡ አጃቢ የፖሊስ አባላት በሚያጅቢቸው በህግ ጥላ ስር የሚገኙ ግለሰቦች ላይ የሚፈፅሟቸው የመጋፋት እና የአካል ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል

ድርጊቶችን የፈፀሙ የፖሊስ አባላትን በወንጀል ጥፋተኛ ለማድረግ መጠቀስ የሚገባው የህግ ድንጋጌ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀፅ 9 ስር የተደነገገው የሥልጣንን አላግባብ መገልገል ድንጋጌ ነው ወይንስ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 424 ስር የተደነገገውን የወንጀል ድንጋጌ ነው? ወይንስ የወንጀል ህግ አንቀፅ 555 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች?

**የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

የሙስና ወንጀል ከሌሎች ወንጀሎች የሚለየው ወንጀሉ የሚፈፀመው በመንግስት የንብረት፣ የገንዘብ ወይም የአደራ ጥቅም ላይ መሆኑ ነው፡፡ የፖሊስ አባላት *የማጀብ* ወይም የመመርመር ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የያዘውን ሰው በተለይም አንድ መግለጫ እንዲሰጠውም ሆነ ጥፋቱን እንዲያምን ወይም ይህንኑ የመሳሰለውን ነገር እንዲገልፅለት ወይም በፈለገው መንገድ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ ለማድረግ አላማ በጥበቃቸው ስር በሚገኛ ሰው ላይ የሚፈፅሙትን ድብደባ በተመለከተ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 424 ስር "በማይገባ አሰራር ዘዴ መጠቀም" በተደነገገው አግባብ እንጂ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት ክስ ሊቀርብ አይገባም፡፡ በሌላ በኩል ከእነዚህ አላማዎች ውጭ በሆነ ምክንያት የፖሊስ አባላት የሚፈፅሙትን የአካል ደህንነት መብት በመጣስ የሚደርስ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀልና በተመለከተ የወንጀል አድራጊነት ተሳትፏቸውን እንደ ጥፋት ማድረግ ሀሳብ እና እንደደረሰው የአካል ጉዳት እና ይህንኑ ለማስረዳት ከሚቀርብ የማስረጃዎች የአስረጂነት ይዘት አንፃር የወንጀል ህጉ አምስተኛ መፅሃፍ ስር (አንቀፅ 555 እና ተከታዮቹ) በተደነገገው በሰው አካል እና ጤና ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚደነግገው የድንጋጌ ክፍል ስር ክስ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

**3.4 በስልጣን አላግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተፈፀመ የሚባለዉ የተሰጠዉን ስልጣን አላግባብ በመጠቀም (Abuse) በማድረግ የተፈፀመ ሲሆን ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት ግን ባለዉ ስልጣን ወሰን ሲፈፀም ስለመሆኑ:- አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9 እና አንቀፅ 13 (1) (ሐ)**

**አከራካሪዉ ጉዳይ፡-** በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለዉ ልዩነት ግልፅ ስላልሆነ የክስ አቀራረብ ልዩነት መኖሩ እና ይህም የፍትሐዊነት ጥያቄ እያስነሳ በመሆኑ፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

ግልጽ በሆነ ሁኔታ ሌላ ሰዉ ለመጥቀም ወይም ራሳቸዉን ለመጥቀም ወይም በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበዉ የተሰጣቸዉን ስልጣን /ኃላፊነት አላግባብ በመጠቀም/Abuse/ በማድረግ የተፈፀመ የሙስና ወንጀል ከሆነ ድርጊቱ በአዋጁ አንቀፅ 9 ስር የሚወድቅና በስልጣን አለአግባብ መገልገል ወንጀል ክስ መቅረብ ያለበት ሲሆን በሌላ በኩል

በተሰጣቸዉ ስልጣን ልክ ወይም ወሰን በአደራ የተሰጣቸዉን እና ሊጠብቁትና ሊከላከሉት የሚገባን የህዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር የፈፀሙ እንደሆነ እና ይህ ደርጊት የተፈፀመዉ የማይገባ ጥቅም ለራሳቸዉ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስገኘቱ ሲረጋገጥ ድርጊቱ በአዋጁ አንቀፅ 13 ስር የሚወድቅና ስራን በማያመች አኳኋን መምራት የሙስና ወንጀል ክስ ሊቀርብ ይገባል፡፡

**3.5 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 15 (1) (ለ) እና አንቀፅ 31) ላይ የተጠቀሰው "በአደራ የተረከበዉ ወይም የሚጠብቀዉ" የሚለዉ ፍሬ ነገር ለሁለቱ ድንጋጌዎች የሚኖረው ተፈፃሚነት**

**አከራካሪዉ ጉዳይ፡-** በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ግልፅ የሆነ መለያ ባለመኖሩ በዐቃቢያነ ህግ መካከል የዉሳኔ አሰጣጥ ልዩነት የሚታይበት እና በዚህ የተነሳ የፍትሐዊነት ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑ፣

**የጠቅላይ ዐ/ህግ አቋም**

በሥራ ተግባር የሚፈጸም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል ስር የተቀመጠዉ "በአደራ የተረከበዉ ወይም የሚጠብቀዉ" የሚለዉ አገላለፅ ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ላይ ከተገለፀዉ "በአደራ የተረከበዉ "ተብሎ ከተገለፀዉ ፅንሰ ሀሳብ ለመለየት የኢፌዲሪ ወንጀል ህግ ሲሻሻል የነበረዉን ነባራዊ ሁኔታ ማየት ያስፈልጋል ይህ ድንጋጌ(በሥራ ተግባር የሚፈጸም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል) በ1949 ዓ.ም ወንጀለኛ መቅጫ ህግ "መስረቅ" በሚል ስያሜ ተገልፆ የነበረ ሲሆን ከመደበኛዉ የስርቆት ወንጀል ጋር እንዳይምታታ ሲባል የተስተካከለ መሆኑን ይገልፃል ስለሆነም ድንጋጌዉ መታየት ያለበት በተለየ ሁኔታ ለአንድ ለተወሰነ አግልግሎት ወይም ጊዜ አንድ ንብረት በአደራ የተሰጣቸዉ ወይም በስራ አጋጣሚ ንብረቱ /ቁሱ/ በእጃቸዉ የገባ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለሆነም በተለየ ሁኔታ ለአንድ የተወሰነ አገልግሎት ወይም ጊዜ በአደራ የተረከበዉን/የተረከበችሁን ንብረት የወሰደ/የወሰደች ወይም የስወሰደ/ያስወሰደች መሆኑ ከተረጋገጠ ክሱ በአንቀፅ 15(1) (ለ) መሰረት መቅረብ ያለበት ሲሆን ከላይ ከተጠቀሰዉ ድንጋጌዉን ለማሻሻል ካስፈለገበት ዓላማ በተለየ መልኩ እምነት ተጥሎበት የተሰጠዉን ንብረት የወሰደ/ያስወሰደ ወይም ያለበትን ቦታ ለማሳየት ያልቻለ ከሆነ ደግሞ ክሱ በአንቀፅ 31 መሰረት ሊቀርብ ይገባል፡፡

**3.6 ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠርና መገልገልን በተመለከተ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/07 አንቀፅ 23/3/ ወይም በወንጀል ህጉ አንቀፅ 378 እና 385 ድንጋጌዎች መሰረት ክስ ስለሚቀርብበት አግባብ**

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** ለተመሳሳይ የድርጊት አፈፃፀም በዐቃቤያን ህግ የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ልዩነት የሚታየው በአዋጁ አንቀፅ 23/3/ ክስ የመመስረት እና በወንጀል ህጉ አንቀፅ 385/1/ እና 378 መሰረት ክስ መመስረት ነው፡፡ ይህም የሙስና ወንጀሎች አዋጅ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎችን ሽሯቸዋል ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባው አዋጁ ነው የሚል እና በሌላ በኩል አዋጁ ግላዊ ሰነዶችና

የምስክር ወረቀቶችን በተመለከተ በግልፅ ያልሻረ በመሆኑ በግልፅ ተለይተው በግላዊ ሰነዶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚመለከት የወንጀል ህጉ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባዋል የሚል ክርክር በመነሳቱ ነው፡፡

## የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም #1

አንድን ሰነድ መንግስታዊ ሰነድ ነው ለማለት ከይዘቱ ባለፈ በመንግስታዊ መዋቅር ስር በሚገኙ ተቋማት የተሰጠ ወይንም የተረጋገጠ ሰነድ ሆኖ የሰነዱ ባለይዞታ ወይንም ተጠቃሚ ሰነዱን ጥቅም ላይ ሲያውለው ይህ በመንግስት የተሰጠ ሰነድ መሆኑ አመኔታ እና የህጋዊነት ማረጋገጫ የሚያስጠው ከሆነ ይህ ማረጋገጫ ከመንግስት ተቋም የተሰጠ በመሆኑ ሰነዱን መንግስታዊ ሰነድ ስለሚያደርገው እነዚህ ሰነዶች ከይዘታቸው ባሻገር ግላዊም ሆነ ተቋማዊ መብትን የሚያረጋግጡ ቢሆንም በባለቤትነት ደረጃ ግን መንግስታዊ ሰነዶች ስለሆኑ እነዚህን ሰነዶች መስራትም ሆነ ሀሰተኛነታቸውን እያወቁ መገልገል የሙስና ወንጀል ተደርጎ በአዋጁ ክስ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

የአዋጁ አንቀፅ 36/2/ በግልፅ *"በወንጀል ህጉ የተደነገጉ ኃላፊነትን አላግባብ መገልገል፣ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ከማግኘት እና ማስገኘት እና በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ከማድረስ ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች"* በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ <u>ተፈፃሚነት አይኖራቸውም</u> በማለት የደነገገ በመሆኑና የወንጀል ህጉ አንቀፅ 385 እና 378 ድንጋጌዎች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ከመነጨ የሀሳብ ክፍል የሚፈፀሙ እና በወንጀል ህጉ ላይም ከዚሁ የሀሳብ ክፍል መነሻነት የሚፈፀሙ በመሆናቸው በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ተፈፃነት የሌላቸው ስለመሆኑ በተዘዋዋሪ የተሻሩ (impliedly repealed) በመሆናቸው በግልፅ በሙስና አዋጁ አንቀፅ 23/3/ ስር ተመሳሳይ ጉዳዮች ክስ ሊቀርብባቸው ይገባል፡፡

## የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም #2

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 378፣ 385 እና ከሙስና ወንጀልች አዋጅ ቁጥር 881/07 አንቀጽ 23 መካከል ያለው ልዩነት የሚመነጨው ከሰነዶቹ ልዩ ባህሪ አንጻር ነው፡፡ ከሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ጋር በተያያዘ እንደ ሰነዱ ይዘት ተለይቶ (የብቁነት ማረጋገጫ፣ ግላዊ ሁኔታ የሚገልጽ) ከሆነ ክሶቹ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 378፣ 385(1) መሰረት ሊቀርብ የሚገባው እንጂ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/07 አንቀጽ 23(3) መሰረት ሊሆን አይገባም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 379 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ በግልፅ የሻረው እና የአዋጁም አንቀጽ 23 ይህንኑ የተሻረውን ድንጋጌ የሚተካ እንጂ በግልፅ ያልተሻረው እና በይዘቱ የተለየ የሰነድ ባህሪ ያላቸውን ሰነዶች የሚመለከተውን የወንጀል ህጉን አንቀፅ 385 የሚመለከት ባለመሆኑና አዋጁም በግልፅ ያልሻረው በመሆኑ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ይህ የወንጀል ህጉ ድንጋጌ ነው፡፡

### 3.7 የኩነቶች ምዝገባ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፤ወደ ሀሰት መለወጥ ወይም መጠቀምን በተመለከተ ከሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/07 አንቀፅ 23 ይልቅ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና በብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ 760/2004 አንቀፅ 66 ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** በሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/07 እና በወሳኝ ኩነት ምዝገባና በብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ 760/2004 መሰረት መንግስታዊ ሰነዶችን አስመስሎ መስራትን፤ወደ ሀሰት መለወጥን ወይም በሀሰተኛ ሰነድ መገልገልን በተመለከተ የሚጣሩ የወንጀል መዛግብት ላይ የሚሰጡ የዐቃቤ ህግ የክስ ውሳኔዎች ጉዳዩ በሁለቱም አዋጆች ስር ሊሸፈን ይችላል በሚል ከፊሉ በሙሰና አዋጁ ክስ ሲያቀርብ ሌላው የኩነቶች ምዝገባ አዋጅን የሚየቀም በመሆኑ ወጥነት ያለው የክስ አቀራረብ ችግር የተፈጠረ መሆኑ ነው፡፡

**የጠቅላይ አቃቤህግ አቋም**

የኩነቶች ምዝገባ ሰነዶችን ለመስጠት ስልጣን በተሰጠው የመንግስት ሰራተኛ ሀላፊ ወይም ሃላፊ አማካኝነት በሀሰት መስለው ቢዘጋጁ ወይም ወደ ሀሰት የመለወጥ ተግባር ተፈፅሞ ቢገኝ ክስ ሊቀርብ የሚገባው ምንም እንኳን የሙስና ወንጀሎች አዋጅ የወጣው በቅርብ ቢሆንም የቀደመውን ህግ በግልፅ በመሻሪያ ድንጋጌው ያልሻረው በመሆኑ፤ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ተሽሯል የሚያስብል የህግ ይዘት በአዋጁ ስላልተገኘ፤ በህግ አተረጓጎም መርህ መሰረት በስራ ላይ ፀንተው የሚገኙ ከአንድ በላይ የሆኑ ህግጋት ሲኖሩ አንዱ ተሽሯል ከመባሉ በፊት በቅድሚያ ሁለቱም ተጣጥመው በስራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ መከተል ስለሚገባ እንዲሁም የህግ አውጭውን ፍላጎትና ለተከሳሽ ጠቃሚ የሚሆነውን ህግ መሰረት ባደረገ መልኩ አንዱ ከአንዱ በቅድሚያ እንዲፈፀም ማድረግ ተገቢ በመሆኑ ከጠቅላላ ከሆነው የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ይልቅ ለጉዳዩ በልዩ ሁኔታ ገዥ በሆነው የከነቶች ምዝገባ አዋጅ ቁ 760/2004 መሆን ይገባዋል፡፡

### 3.8 በሙስና የማታለል ወንጀልና ከሙስና ወንጀል ውጭ ሌሎች የማታለል ወንጀሎችን በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 32 እና የወንጀል ህግ አንቀፅ 696 የተፈፃሚነት ሁኔታ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** በመንግስት ሰራተኛ አማካኝነት የሚፈፀምን ከባድ የአታላይነት ወንጀል በተመለከተ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 696 እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/2007 በተደነገገው መሰረት የቅጣት ልዩነት በመኖሩ እንዲሁም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 696 የአፈፃፀም ገደብ እንዲኖረው የተደረገ ቢሆንም በተመሳሳ ጉዳዩች ዐቃብያነ ህግ የክስ አቀራረብ ልዩነት የፈጠሩ ከመሆኑ ባለፈ በፍርድ ቤት ተደጋጋሚ የክስ ይሻሻል ትዕዛዝ እየተሰጠ የሚገኝ መሆኑ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የወጥነት መጓደል መስተዋሉ ነው፡፡

**የጠቅላይ አቃቤ ህግ አቋም**

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 22 እና በወንጀል ህግ አንቀፅ 6 መሰረት አንድን ድርጊት በተለያዩ ጊዜ የወጡ ህግጋት ወንጀል የሚያደርጉት ሆነው አንዱ ሌላውን የሻረው ወይም የአፈፃፀም ገደብ አድርጎበት እንደሆነ ክሱ መቅረብ ያለበትና አጥፊውም የሚቀጣው ቅጣቱ ቀላል በሆነው ህግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህም_የማታለል ድርጊቱ በመንግስት ሰራተኛ የተፈፀመባቸው በተለይም የድርጊቱ አፈፃፀም ቀላል የሆኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ማናቸውም የሙስና ወንጀሎች ክስ ሊቀርብ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 32 መሰረት ነው፡፡ ይህ የክስ አቀራረብ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ከወጣ በኂላ የተፈፀሙ ድርጊቶችን ብቻ ሳይሆን አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 696 ስለሙስና ወንጀሎች ጉዳይ በስራ ላይ በነበረበት ( አፈፃፀሙ ባልተገደበበት ) ጊዜ ተፈፅመው እስከዛሬ ክስ ያልቀረበባቸውና የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜው ባላለፈባቸው ጉዳዮች ላይ ጭምር ይሆናል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ ድርጊቱ ቀድሞ የነበረው ህግ በስራ ላይ በነበረበት ወቅት የተፈፀመ በከባድ አፈፃፀም የወንጀል ተግባር ክስ የሚቀርብበት ከሆነ ከአዲሱ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ይልቅ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 696 ከመነሻ ቅጣት አኳያ የተሻለ በመሆኑ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ከወንጀል ስነ-ስርዐት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የአተረጓጎም ልዩነት የፈጠሩ ድንጋጌዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ

### 4.1 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 60(ሐ) በአንቀጽ 665(1) እና 559(2) ላይ ስለሚኖረው ተፈፃሚነት

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** አንድ ግለሰብ የተለያዩ ሰዎችን ተንቀሳቃሽ ንብረት ይዞ የስርቆት ወንጀል ቢፈፀምበት እና የራሱን ንብረት ጨምሮ የሌሎቹም ሰዎች ንብረት ቢወሰድ ድርጊቱን የፈፀመው ግለሰብ አንድ ወንጀል ፈፅሟል ነው ሊባል የሚችለው ወይስ በእያንዳንዱ ባለንብረት ልክ የተናጠል ክስ ሊቀርብበት ይገባል?

የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60(ሐ) እና 559(2) በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ላይ ሰበር የሰጠውን ትርጉም ተከትሎ ዓ/ሕግ ክስ ማቅረብ አለበት ወይስ በጉዳዩ ላይ ሌላ አይነት ትርጉም ለማሰጠት ተደራራቢ ክስ መመስረት አለበት?

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

**በመጀመሪያው ጭብጥ ላይ** ለወ/ህግ 665(1) ማቋቋሚያ ተከሳሹ የሌላን ሰው ንብረት አዩኝ አላዩኝ ብሎ መውሰዱን ከማረጋገጥ ውጭ የድርጊቱ ፈፃሚ የንብረቱን ባለቤቶች ማወቁን ወይም ግንዛቤው ያለው ስለመሆኑ  የማስረዳት ግዴታ ስለማይጥልና በወ/ሕግ 60(ሐ) መሰረት ደግሞ ድርጊቱ በአንድ አይነት ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት ተፈፅሞ አንድን የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ ቢሆንም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ጥቅም ላይ ጉዳት ካደረሰ ጉዳት በደረሰባቸው ሰዎች ልክ ተደራራቢ ክስ ሊመሰረት እንደሚገባ ስለሚጠቁም፤ አንድ ግለሰብ የተለያዩ ሰዎችን ተንቀሳቃሽ ንብረት ይዞ የስርቆት ወንጀል ቢፈፀምበት እና የራሱን ንብረት ጨምሮ የሌሎቹም ሰዎች ንብረት ቢወሰድ ድርጊቱ ፈፃሚ በእያንዳንዱ ባለንብረት ልክ የተናጠል ክስ ሊቀርብበት ይገባል፡፡

**ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ**

በወ/ሕግ 60(ሐ) ላይ በአንድ ወንጀል ሀሳብ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ላይ ጉዳት በሚያደርስበት ወቅት ተደራራቢ ወንጀል እንደሚሆን ስለሚስረዳ፤ የወ/ህጉ አንቀፅ 559(2) የአንቀፅ 60(ሐ) ልዩ ሁኔታ ተደርጎ ስላልተቀመጠ እና ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች ከአንድ በላይ ሲሆኑ ሕጉ የተለየ ቅጣት ስላላስቀመጠ፤ የሰበር ችሎትም የወ/ሕግ አንቀፅ 559(2) በተመለከተ ትርጉም የሰጠበት መንገድ ስህተት በመሆኑ ዓ/ሕግ በዚህ ጉዳይ ላይ በተጎጂዎች ቁጥር ልክ ተደራራቢ ክስ መመስረት ይገባዋል፡፡ ክሱን የሚያየው ፍ/ቤት ሰበር ችሎቱ ከሰጠው የሕግ ትርጉም አንፃር መርምሮ የሚከሰሰውን ግለሰብ ጥፋት በአንድ በመጠቅልል ቅጣት ከወሰነ ይህንን መሰረታዊ የሕግ ስህተት

ጠቅሶ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ይግባኙን በማቅረብ ጉዳዩን ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ችሎት ጉዳዩ እንዲታይ ማስደረግ አለበት፡፡

## 4.2 በዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የሕጋዊ መከላከል መስፈርቶች ከተሟሉ ክስ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** የወ/ሕግ 78፣ ሕጋዊ መከላከልን መሰረት አድርጎ የተፈፀመ ድርጊት በወንጀል ጥፋተኛ አያስብልም ሳይሆን በወንጀል አያስቀጣም በሚል ስለተቀረፀ በዓ/ህግ በኩል የተሰበሰቡት ማስረጃዎች የሕጋዊ መከላከልን መስፈርት አሟልተው ቢገኙም አንዳንድ ዓ/ሕግ የወንጀል ቅጣት የሚመጣው ከፍርድ ቤት የክርክር ሂደት በኋላ ነው በሚል በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ክስ የሚመሰረትበት ሁኔታ መስተዋሉ ከፊሉ ዓ/ሕግ ደግሞ ሕጋዊ የመላከል ድርጊትን ያሟላ መዝገብን በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 42(1ሀ) የሚዘጉ መሆኑ በዚህም የውሳኔ ወጥነት ችግር የፈጠረ ስለመሆኑ

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 42(1ሀ) መሰረት አንድን ተጠርጣሪ ጥፋተኛ ለማስደረግ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ከሌለ ዐቃቤ ሕግ ክስ ማቅረብ እንደሌለበት ተደንግጓል ይህም ማለት ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ሲመዝን ጥፋተኛ የሚያስደርግ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ መከላከል የያዛቸው መስፈርቶች በአንድ ጉዳይ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ከተሟሉ ተከሳሽን ጥፋተኛ አስብሎ ማስወሰን ስለማይቻል በአንድ ጉዳይ ውስጥ ሕጋዊ መከላከል መሟላቱ ዓ/ህጉ ካረጋገጠ ወንጀል ሕጉ አላማን ከማሳካት አንፃር ክስ አይቀርብም የሚል ውሳኔ መስጠት አለበት ነገር ግን ወንጀሉ በወ/ሕጉ 79 ባስቀመጠው መሰረት ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ መሆኑ ከተረጋገጠ ዓቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ ክስ መመስረት አለበት፡፡

## 4.3 ፈጻሚው ባልታወቀ ተጠርጣሪ ላይ የተጣራ የምርመራ መዝገብ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 42(1) (ሀ) መሰረት ሊዘጋ የሚገባው ስለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** ፈጻሚው ባልታወቀ ሰው የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞ ፖሊስም ምርመራውን አጠናቆ የምርመራ መዝገቡ ለዐቃቤ ሕግ በሚቀርብበት ጊዜ በአንድ በኩል በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 42(1)(ለ) የተከሰሰውን ሰው ለማግኘት የማይቻል ወይም በሌለበት ክሱ ሊታይ የማይቻል የሆነ እንደሆነ በሚል በአማራጭ ያስቀመጠው ስለሆነ ፈጻሚው ያልታወቀውንም ያካታል በሚል ይህንኑ ድንጋጌ በመጥቀስ መዝገብ ሲዘጋ በሌላ በኩል ፈጻሚው ያልታወቀው በማስረጃ ማጣት ምክንያት ስለሆነ የአያስከስስም ውሳኔው ሊሰጥ የሚገባው የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ  በመጥቀስ ነው የሚል መከራከሪያ መኖሩ፡፡

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

ከወ/መ/ስ/ስ/ሕጉ ቁጥር 42(1) (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች አወቃቀር መገንዘብ እንደሚቻለው የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (ለ) ተግባራዊ የሚሆነው የምርመራ መዝገቡ ሲመረመር የወንጀል ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በቂ ማስረጃ ኖሮ እና የፈጻሚው ማንነትም በማስረጃ ተረጋግጦ ነገር ግን ፈጻሚውን ለማግኘት የማይቻል ሲሆን እና ክሱም በሌለበት የማይታይ ሲሆን ነው፡፡ ፈጻሚው አለመገኘቱ እና እርሱ በሌለበት ክሱ ሊታይ አለመቻሉ ተጣምረው ሊነበቡ ይገባል እንጂ እያንዳንዱ ነጥብ በተናጠል ክስ አላቀርብም ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ ይልቁንም ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን መርምሮ የቀረበው ማስረጃ የወንጀል ድርጊቱ መፈጸሙን በበቂ ሁኔታ የሚያረጋግጥና ማን እንደፈጸመውም የሚያሳይ ከሆነ ቀጣዩ ስራው ክሱ ተከሳሹ በሌለበት ሊታይ የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በማረጋገጥ በሌለበት ሊታይ የማይችል ከሆነ የአያስከስስም ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 15 ባልታወቀ ሰው ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወይም የክስ አቤቱታ አቤቱታ አቅራቢው ወንጀለኛውን ለይተው የሚያሳውቁትን ልዩ ልዩ ምልክቶች ሁሉ በዝርዝር መስጠት ያለበት መሆኑን መደንገጉ ሲታይ እነዚህን ምልክቶች መሰረት በማድረግ በሌሎች ማስረጃዎች የፈጻሚውን ማንነት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ ይህ ድንጋጌ በዚሁ የወ/ስ/ስ/ሕ/ቁ/ 111(1)(ሀ) ስር በማንኛውም የክስ ማመልከቻ ላይ የተከሳሹ ስም የግድ መገለጽ እንዳለበት መደንገጉ በጣምራ ሲታይ የተጠርጣሪውን/ፈጻሚውን ማንነት ለይቶ ማወቅ የማስረጃ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የፈጻሚው ማንነት በማስረጃ ካልተረጋገጠ የምርመራ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባው በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 42(1)(ሀ) መሰረት ሲሆን የፈጻሚው ማንነት እና ድርጊቱንም መፈጸሙን በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦ ነገር ግን ፈጻሚውን ማግኘት ካልተቻለ እና ጉዳዩም በሌለበት ሊታይ የማይችል ከሆነ የምርመራ መዝገቡ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 42(1) (ለ) መሰረት ሊዘጋ ይገባል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዐቃቤ ሕግ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 42(1) (ሀ) እና (ለ) ስር ከተደነገገው ውጭ ሕጋዊ ፍሬ ነገር ስላልተሟላ የወንጀል ተጠያቂነት የለም የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) እና በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/08 አንቀጽ 6(3) (ሀ) መሰረት ሊዘጋ/ሊቋረጥ/ ይገባል፡፡

## 4.4 በህግ በግልፅ ባልተፈቀዱ ጉዳዮች የተከሳሽ የቀድሞ ጥፋተኛነት ለዋስትና ክርክር መነሳት የሌለበት ስለመሆኑ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-**ሕጉ በተለይ በግልፅ ካልፈቀደ በቀር በፍርድ ጥፋተኛነት ከመታወቁ በፊት ተከሳሹ ከዚህ በፊት ተከሶ የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ አይገለፅም ብሎ የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 138 ቢደነገግም በአንድ በኩል ይህ ድንጋጌ የወ/ስ/ስ/ሕ/ቁ **67(ለ)** ላይ የተመለከተውን አንስቶ የተከሳሽን ሪከርድ ለፍ/ቤት በማቅረብ የዋስትና መከራከሪያ ከማድረግ የሚገድብ አይደለም በሚል የተከሳሽን

ሪከርድ የዋስትና ክርክር ግዜ የመጠቀም ልምድ ያለ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 138 ግልፅ ክልከላ አስቀምጧል በሚል የተከሳሽን የወንጀል ሪከርድ ከፍርድ በፊት የማይነሳበት ሁኔታ መኖሩ በዚህም ወጥ ያልሆነ አሰራር መኖሩ

**የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቋም**

በወ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 67(ለ) መሰረት የተያዙ ሰዎች ሌላ ወንጀል ይፈፅሙ ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን የዋስትና ጥያቄያቸው ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል ያስቀምጣል ነገር ግን ይህ ድንጋጌ በስነስርዐት ህጉ ቁጥር 138(1) በተቀመጠው አግባብ ዓ/ሕግ የተከሳሾችን የቀድሞ ጥፋተኛነት ሪከርድ አቅርቦ እንዲከራከር የሚፈቅድ ግልፅ ሕግ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67(ለ) ስር የተደነገገው የዋስትና መብት ገደብ በተከሳሹ ያለፈ የወንጀል ታሪክ ላይ የሚመሰረት አይደለም፡፡ ይልቁንም የድንጋጌው ዓላማ በእጅ ላይ ያለውን የክሱ ሂደት ሊያደናቅፍ ይችላል ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ በዋስ የመለቀቅ መብቱን ለመገደብ የተደነገገ ነው፡፡በአጠቃላይ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 138(1) የተከሳሽን ንፁሕ ሆኖ የመገመት ሕገመንግስታዊ መብት የሚያመለክት በመሆኑና ዳኞች የወንጀል ጉዳይ በሚመረምሩበት ጊዜ በተከሳሹ የጥፋተኝነት ሪከርድ ጫና አድርጎባቸው የተሳሳተ ውሳኔ እንዳይሰጡ ለማድረግ ታስቦ የተደነገገ በመሆኑ ህጎች በግልፅ ባለፈቀደባቸው ጉዳዮች ላይ ዓቃቤ ሕጎች የተከሳሽ(ሾች)ን የቀድሞ ጥፋተኛነት አንስተው የዋስትና ክርክር ማድረግ የለባቸውም፤ ከዚህ ውጭ የተከሳሽ የወንጀል ሪከርድ ቅጣትን የሚያከብድ ወንጀል ብቸኛ ማቋቋሚያ ሆኖ ከተገኘ ዓ/ሕግ የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 114(1) ን ተከትሎ ተከሳሹ ከዚህ ቀደም ጥፋተኛ መሆኑን የሚያመለክት ነገር ክሱ ላይ ሳይጠቅስ ቅጣትን የማያከብድ የወንጀል ክስ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ያቀረበውን ክስ ጥፋተኛ ካስባለ በኋላ ግን የወ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 114ን መሰረት አድርጎ ተከሳሹ ቀድሞ የተቀጣበትን ማስረጃ ለፍ/ቤቱ በማቅረብ ቅጣቱ በሚከብድበት ወንጀል ቅጣት ማሰጠት አለበት፡፡

## 4.5 ተከሳሽ በሌለበት ክሱ እንዲታይ በሚቀርብ አቤቱታ የግድ ተከሳሹ የተከሰሰበት ክስ መነሻ ቅጣቱ አስራ ሁለት አመት ጽኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ስላለመሆኑ፡ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161/2/ሀ

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ከቁጥር 160 እስከ 166 ባሉት ድንጋጌዎች ስር ተከሳሹ በሌለ ጊዜ ስለሚፈጸም ስነ ስርዓት የደነገገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በቁጥር 161/1/ ተከሳሹ ያለ በቂ ምክንያት ነገሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን የቀረ እንደሆነ አለመቅረቡን ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ከጻፈ በኋላ በዚህ ክፍል በተጻፈው መሰረት ነገሩ እንዲሰማ ያዝዛል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ተፈጻሚ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች ውስጥ ደግሞ በቁጥር 161/2/ሀ ስር ''ከአስራ ሁለት አመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ" በሚል የተደነገገውን ድንጋጌ በተመለከተ ህጉ በመተርጎም ሂደት አከራካሪ እና ቁርጥ ያለ አቋም ለመያዝ የሚያስቸግር ነው፡፡ በአንድ በኩል ይህ

ድንጋጌ ስለመነሻ ቅጣት እንጂ ስለመድረሻ ቅጣት የሚገለፅ ባለመሆኑ መነሻ ቀጣቱ አስራ ሁለት አመት ጽኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ካልሆነ በስተቀር ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት መታየት የለበትም የሚል ክርክር የሚያስነሳ ሲሆን ቤላ በኩል ደግሞ የአስራ ሁለት ዓመት ፅኑ እስራት ዝቅተኛው የቅጣት መጠን መሆኑ አስገዳጅ አይደለም፤ቅጣቱ በዝቅተኛውና በከፍተኛው ቅጣት መካከል የሚገኝ ከሆነ ተከሣሽ በሌለበት ጉዳዩን ማየት ይቻላል በማለት የሚከራከሩ አሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ይህን ድንጋጌ በመተርጎም ሂደት የወጥነት ችግር እንዲፈጠር ሆኗል፡፡

## የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም

ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክሱን ማየት በሕግ የተከለከለ ባይሆንም ጉዳዩ እንዲቀጥል ፍርድ ቤቶች የሚወስኑ ከሆነ የተከሳሹን መብት በማያጣብብ መልኩ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ረገድ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161/2/ሀ ስር "ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ እንደሆነ" የሚለው መነሻ ቅጣትን ወይስ የ12 አመት እስራት ቅጣት በዝቅተኛውና በከፍተኛው ቅጣት መካከል የሚገኝ የሚለው በፌደራላ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚችሎት የሚሰጣቸው ውሳኔዎችን ጨምሮ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ መግባባት ላይ ያልተደረሰበት ጉዳይ ነው፡፡

በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስር ያሉ ዐቃብያነ ህግ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161/2/ሀ ስር "ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ እንደሆነ" የሚለው መነሻ ቅጣትን ወይስ የ12 አመት እስራት ቅጣት በዝቅተኛውና በከፍተኛው ቅጣት መካከል የሚገኝ በሚል እየተስተዋለ ላለው የህግ አተረጓጎም ልዩነት የተከሳሽ መብትም አላግባብ እንዳይጣስ ሁለቱን ባስታረቀ መልኩ መነሻ ቅጣታቸው 12 ዓመት በሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ተከሳሽ በሌለበት ክሱ መሰማቱ እንዲቀጥል መነሻ ቅጣታቸው ከ12 ዓመት በታች በሆኑ ወንጀሎችን በተመለከተ በተከሳሽ ላይ የቀረበው ክስ በእርግጥም የሚወሰነው ውሳኔ 12 ዓመትና ከዚያ በላይ የሚያስቀጣው መሆኑን የቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት እንዲሁም ደረጃ እና እርከን ባልወጣላቸው የወንጀል ዓይነቶች ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበት ክስ የ12 ዓመት የእስራት ቅጣቱ በዝቅተኛውና በከፍተኛው ቅጣት መካከል የሚገኝ በሚሆንበት ጊዜ ደገሞ በተከሳሽ ላይ ጥፋተኛ ቢባል 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ሊቀጣ የሚችል ከሆነ ተከሳሹ በሌለበት ክሱ መሰማቱ እንዲቀጥል ዐቃቤ ህግ ሙያዊ ክርክር ሊያደርግ ይገባል፡፡

4.6 በጊዚያዊነት በሚሰጡ ትእዛዞች ላይ ይግባኝ ስለሚጠየቅበት ሁኔታ

**የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር184**

**አከራካሪው ጉዳይ:-** የወንጀል ይግባኝ አቤቱታ እና ክርክሮች ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል የተወሰኑ ጉዳዮች የይግባኝ ምክንያት እንዳይሆኑ የወንጀል ስነ ስርዓት ህጉ ክልከላ ወይም ገደብ አስቀምጦ ይገኛል። የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 184 የትዕዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ በሚል ርዕስ በቀጠሮ መስጠት ወይም አለመስጠት፣ በወንጀል ክስ በሚቀርቡ መቃዎሚያዎች ላይ በሚሰጥ ብይን እና በክርክሩ ሂደት በሚቀርብ ማስረጃ ወይም የሚቀርቡ ምስክሮች ምስክር ቃል አቀባበል ላይ በሚሰጥ ብይን ላይ ይግባኝ የማይፈቀድ ስለመሆኑ የተደነገገውን በሚገባ በመረዳት በኩል ልዩነቶች መፈጠር እና ተከሳሽ በሌለበት ክስ እንዲታይ በሚቀርብ አቤቱታ እና ማስረጃ ስለመቀበል ወይም ስላለመቀበል በሚቀርብ አቤቱታ የሚሰጥ ውሳኔን በጊዜያዊ የሚሰጡ ትእዛዞች ናቸው በሚል ይግባኝ የማይጠየቅበት ሁኔታ መፈጠሩ

**የትዕዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 184**

በጊዜያዊነት በሚሰጡ ትእዛዞች ላይ ይግባኝ የማይባል ስለመሆኑ በወንጀል ስነ ስርዓት ህጉ ተደንግጎ ይገኛል።

*ቁጥር 184 የትዕዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ*

*ከዚህ በታች ባሉት ሁኔታዎች ፍርድ ቤት በሚሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ ማለት አይቻልም።*

*ሀ. በቁጥር 94 መሰረት ቀጠሮ መስጠት ወይም አለመስጠት ወይም*

*ለ. በቁጥር 131 መሰረት ስለሚቀርብ መቃወሚያ ወይም*

*መ. በቁጥር 146 መሰረት ማስረጃ ስለመቀበል ወይም ስላለመቀበል።*

*ነገር ግን የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ውሳኔ፣ ለጊዜው በመለቀቅ ወይም ነጻ በመለቀቅ ፍርድ ተሰጥቶ ይግባኝ በተባለ ጊዜ እነዚህ የተሰጡት ትእዛዞች ይግባኝ ለማለት ምክንያቶች ለመሆን ይችላሉ።*

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተጠቀሱት ይግባኝ ለማለት የተከለከለባቸው ምክንያቶች የአንቀጹ አቀራረጽ በግልፅ ባያሳይም ጊዜየያዊ አገልግሎት ያላቸውን ትእዛዞች የሚመለከት ነው። ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸውን ትእዛዞች ላይ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ይግባኝ እንዳይባል የተፈለገበት አላማ በዋናነት የይግባኝ ስርዓቱ ጊዜያዊ አገልግሎት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ተንጠልጥሎ ቅልጥፍናና ውጤታማነቱ እንዳይቀንስ ለማድረግ ነው።

የትእዛዝ ይግባኝ የለም ማለት ግን እነዚህ ትዕዛዞች ሙሉ ለሙሉ የይግባኝ ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም ማለት አይደለም፡፡ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጊዜ ጊዜያዊ አገልግሎት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የተሰጠ ትእዛዝን መሰረት በማድረግ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ የአንቀጽ 184 የመጨረሻው አረፍተ ነገር በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡

በአንቀጽ 184 በትእዛዝ ላይ ይግባኝ ስላለመኖሩ በሚል የተደነገገው ድንጋጌ በአንድ በኩል የቃላት አገባብ ችግር ያለበት መሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ የተቀመጡ ክልከላዎች ጥቅል በመሆናቸው ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ በመዝገቡ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በሚገባ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የተሰጠው ትእዛዝ መዝገቡ እንዲዘጋ አልያም ነጻ እንዲወጣ የሚያደርግበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡

በአንቀጽ 184 (ሀ) በቁጥር 94 መሰረት ቀጠሮ መስጠት ወይም አለመስጠት ይግባኝ ሊባልበት አይችልም በሚል በጥቅል ያስቀመጠ ቢሆንም በቁጥር 94 (2)(ሀ) ዐቃቤ ህጉ፣ የግል ከሳሹ ወይም ተከሳሹ በበቂ ምክንያት ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ሊሰጥ እንደሚችል የተመለከተውን ዐቃቤ ህጉ ወይም ተከሳሹ በበቂ ምክንያት ሳይቀርቡ ስለመቅረታቸው አላሳመነኝም በሚል መዝገቡ ቢዘጋ ወይም ደግሞ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ሆኖ ዐቃቤ ህግም ይህንን አሳስቦ እያለ ፍርድ ቤቱ መዝገቡ እንዲዘጋ ቢያዝዝ ይሄ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ነው በሚል ሊታለፍ የሚገባው ባለመሆኑ በዚህ አግባብ በተሰጡ ትእዛዞች ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ የመጠየቅ ሙያዊ ግዴታ አለበት፡፡

በተመሳሳይ በአንቀጽ 146 ማስረጃን ስለመቃወም በሚል በተደነገገው ስር የሚሰጥ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ አይገባም በሚል በአንቀጽ 184 (መ) ስር የተገደነገገው በአጠቃላይ በመዝገቡ ላይ የሚኖረው ሁኔታ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ በዐቃቤ ህግ የቀረበን  ማገጃ ተከሳሹ ሊቀርብ አይገባም በሚል ቢቃወም እና ፍርድ ቤቱም በዚህ አግባብ ማስረጃውን ውድቅ ቢያደርግ ይህ በመዝገቡ ውጤታማነት ላይ በቀጥታ የመወሰን እጣ ፈንታ ያለው ከሆነ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትእዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ በእንደዚህ አይነት ትዕዛዞች ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አተቋም

ዐቃቤ ህግ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 184 የትእዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ የሚለው ጊዜያዊ አገልገሎት ባለቸው ትዕዛዞችን እንጅ የመዝገቡን አጠቃላይ ውጤታማነት በሚመለከት የሚሰጡ ትዕዛዞች ላይ ከሆነ ይግባኝ ሊጠይቅ ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተከሳሽ በሌለበት መዝገብ እንዲታይ በሚል የሚቀርብ የዐቃቤ ህግ አቤቱታ በፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጎ መዝገቡ ለጊዜው የመቋረጥ ውሳኔ ጊዜአዊ

አገልግሎት ያለው ትእዛዝ ባለመሆኑ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ሊጠይቅበት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በተመሳሳይ የዐቃቤ ህግን ማስረጃ በአንቀጽ 146 አግባብ ውድቅ ማድረግ የመዝገቡን እጣፋንታ የሚወስን ስለሚሆን ማስረጃ የመስማት ሂደቱ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በማድረግ ይግባኝ ሊጠይቅ ይገባዋል እንጂ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 184 አግባብ ይግባኝ አያስብልም ተብሎ ታልፎ በመጨረሻ መዝገቡ ውሳኔ ሲያገኝ አብሮ ይግባኝ ይጠየቅበታል በሚል ሊተለፍ የሚገባው አይደለም፡፡

**4.7 በወንጀል ህጉ በግልጽ በግል አቤቱታ ከሚቀርቡ ወንጀሎች ውጪ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች በእርቅ የማይቋጩ ስለመሆናቸው፡ የእርቅ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2012፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 211፣ 212፣ 664፣580 እና 590(1)**

**አከራካሪው ጉዳይ፡-** በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ ወንጀልች ወንጀሉ ከብዶ በከባድ ሁኔታ ክስ እንደሚቀርብ ተደንግጎ እያለ በወንጀል ህጉ ወንጀሎቹ በግልጽ በግል አቤቱታ የያስቀጡ መሆናቸው ባልተደነገገበት ሁኔታ ጉዳዮችን በእርቅ እንዲቋጩ መደረጉ፤ ከዚሁ ጋር ተያያዝነት ባለው መልኩ የወንጀል ህግ አንቀጽ 664 መሰረት በማድረግ በቤተ ዘመድ አባሎች መካከል እንደ ውብድበና፣ መንጠቅ ወይም ማስፈራራት፣ ከመሳሰሉት በሀይል ወይም በማስገደድ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች በስተቀር ሌሎች ሌሎች ወንጀሎች ሲደረጉ ጉዳዩ የሚታየው በግል አቤቱታ ነው የሚለውን ከእርቅ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 3 እና 4(1) መሰረት በማድረግ በአካል ጉዳት ማድረስ የሚፈጸሙ በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በእርቅ ማለቅ ይችላሉ የሚል አመለካከት መፈጠሩ

**ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቋም**

በእርቅ አፈጻጸም መመሪያው እርቅ የሚፈቀደው ጉዳታቸው ከህብረሰቡ ጥቅም ይልቅ የተበዳዩን ግለሰብ ጥቅም እና ደህንነት የሚመለከቱ በመሆናቸዉ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ስለመሆኑ በግልጽ በተደነገጉ ወንጀሎች ነው፡፡ በህጉ በግልጽ በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ ስለመሆናቸው ያልተደነገጉ ወንጀሎችን የወንጀል ህጉን አንቀጽ 664 በመጥቀስ ጉዳዩን በእርቅ መጨረስ የእርቅ አፋጻጸም መመሪያውን እና የወንጀል ህጉን አንቀጽ 664 ያላገናዘበ በመሆኑ በዚህ አግባብ እርቅ ሊፈጸም አይገባም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 664 ተፈፃሚ የሚሆነው በቤተ ዘመድ አባሎች መካከል እንደ ውብድበና፣ መንጠቅ ወይም ማስፈራራት፣ ከመሳሰሉት በሀይል ወይም በማስገደድ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች ወጪ በሆኑ በንብረት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች እንጅ በአካል ጉዳት ማድረስ ወይም በሌሎች ወንጀል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በወንጀል ህጉ ተፈጸመ የተባለው ወንጀል በግልጽ በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ መሆኑ እስካልተደነገገ ድረስ ወንጀሉ የሚያስቀጣው በወንጀል ክስ አቅራቢነት ነው፡፡ በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ ወንጀሎች

በልዩ ሁኔታ ወንጀሉ ከብዶ እንደሚያስቀጣ በሚደነገግበት ወቅት ለምሳሌ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 618(1) በተገለጸው አግባብ በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚያስቀጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 590(1) ስር ከባድ የዛቻ ወንጀል ሲፈጸም ጉዳዩ በእርቅ ሊቋጭ የሚችል አይደለም፡፡